# ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

<u>አዘጋጅ</u>

ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ

<u>አሳታሚ</u> ፡ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት

አዲስ አበባ
1983 ዓ/ም

www.ethiopianorthodox.org

በሐዲሱ ግን ጽላትም ታቦትም የሚባለው ያው አንዱ ምሥዋዕ ነው፤ጽላት ሲቀረጽ ጻሕል ጽዋዕ እንዲይዝ ከቦታ ወደ ቦታ ለማዛወር እንዲቻል ሆኖ ይቀረጻል ። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፩.) ከዚህ በኋላ በጽላቱ ላይ አልፋ ወኦ ቤጣ የውጣ የሚለው የጌታ ስም ይቀረጽበታል ፤ ከላይ ሥዕለ ሥላሴ ቀጥሎ ምስለ ፍቁር ወልዳ፥ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ፥ እንዲሁም መቅደሱ የተሠራለት ጻድቅም ሆነ ሰማዕት ሥዕሉ ይቀረጻል ስሙ ይጻፋል ።

ሐ. ጽላተ ኪዳኑም ማኅደረ እግዚአብሔር ነው ያለ ታቦትም መሥዋዕት አይሠዋም ።

## ማኅቶተ ቤተ ክርስቲያን (የቤተ ክርስቲያን መብራት)

ሀ. በቤተ ክርስቲያን የሚበራው መብራት ጧፍና ዘይት ነው፤ (ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፩) ።

ለ. በቤተ ክርስቲያን ብዙ መብራት ማብራት ታዝዟል በተለይ ቅዱሳት መጻሕፍት ማለት ጳውሎስ ፥ መልእክታተ ሐዋርያት ፥ ግብረ ሐዋርያት ሲነበቡ ቤተ ክርስቲያኑ በጣም የበራ እንዲሆን ታዝዙዋል ። ይልቁንም ወንጌል ሲነበብ እጅግ በጣም መብራት ማብዛት እንደሚገባ ተሠርቶአል ። (ፍት ፡ አን ፡ ፩ ።

## ሥርዓተ መቅደስ ወዐውደ ምሕረት

ሀ. በታቦት ፊት ለመስገድ ለመጸለይ ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው ወደ መቅደስ ገብቶ እንዲቀመጥ አልተፈቀደለትም ።



ለ. ካህን ካልሆነ በስተቀር ከምእመናን ወገን ማንኛውም ሰው ወደ መቅደስ ገብቶ ሥጋ ወደሙ አይቀበልም ወደ ታቦትም አይጠጋም (ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፩ በደስ ፲፱) ።

ሐ. ሴቶች ወደ መቅደስ እንዲገቡና በመቅደስ ውስጥ እንዲጸልዩ አልተፈቀደም (ፍት፡ ነገ ፡ አን ፡ ፩ ፡ ዶቅ ፡ ፵፩) ።

መ. በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽረ ግቢና የውጭ ዐደባ ባይ ገበያ ክልክል ነው። ኤር፡ ፯፡ ፲፩፡ ማቴ. ፳፩፡ ፲፪ - ፲፫ ። ማር፡ ፲፩ ፡ ፲፭-፲፯ ። ሉቃ ፡ ፲፱ ፡ ፵፭—፵፮ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፫—፲፰ ፡ ፍት ፡ ነገ ፡ ፩ ።

ሠ. በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በቅጽረ ግቢም ቢሆን ግብዣ ማድረግ መብላት መጠጣት ክልክል ነው ፤ (ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፩ ፡ ዶቅ ፡ ፳፰ ።

ረ. ከቤተ ክርስቲያን የገባና የተቀደሰውን ንዋየ ቅድሳት እንደገና ወደውጭ አውጥቶ ለሥጋዊ አገልግሎት ማዋል አይገባም (ፍት ፡ ነገ ፡ አን፥ ፩ ፡ ረስጣ ፡ ፳፰) ።

ሰ. ያላመኑ ፡ ያልተጠመቁ ፡ ተወግዘው ፡ የተለዩ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገቡ ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያንን እንዳይሳተፉ ተከልክሏል የቤተ ክርስቲያኑ በሮችም በአጋፋሪዎች እንዲጠበቁ ታዝዞአል (ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፩ ፡ ድስቅ ፡ ፲፪)

www.ethiopianorthodox.org

## ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ የሚደረግ ጥንቃቄ

ሀ. ወደ ቤተ ክርስቲያን ለጸሎትና ቅዱስ ቊርባንን ለመቀበል በሚኬድባቸው ዕለታት እንዲሁም በጾም በሰንበትና በበዓላት ቀኖች ወንድና ሴት መገናኘት ክልክል ነው ፤ በመኝታ የተገናኘ ወደ ቤተ ክርስቲያን በዕለቱ አይገባም ፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ባይሄዱም በዓላትን አጽዋማትን ሊጠብቁ ይገባል ዘፀ ፡ ፲፱ ፡ ፲፭ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፭—፯) ።

ለ. ለሐ ጩን ንፍጡን የማዝረብረብ ነውር ያለበት በዚህ ነውር ላይ እያለ ወደ ቤተ ክርስቲያን አይገባም ሥጋ ወደሙም ሊቀበል አይገባውም (ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፲፫)

ሐ. ሴት የወር አበባዋ (መርገሟ) ሲመጣ እስከ ሰባት ቀን ድረስ ፡ ስትወልድ ወንድ ከወለደች እስከ ፵ ቀን ሴት ከወለደች እስከ ፹ ቀን ድረስ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳትገባ ክልክል ነው፤ ከዚህ በኋላ ግን ገላዋን ታጥባ ትገባለች (ዘሌዋ ምዕ ፡ ፲፪ ። ፲፭ ፡ ፲፱—፳፰ ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፮ ፡ ዘኂቅያ ፡ ፷፱ ፤

መ. ወንድ ሕልመ ሌሊት(ዝንየት)ከመታው በዕለቱ ወደቤተ ክርስቲያን አይገባም በማግሥቱ ገላውን ታጥቦ ይገባል (ዘሌ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮-፲፰)



## ቤተ ክርስቲያን ሲሳለሙ

ሀ. ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ በር ላይ ሲደርሱ መሳለም ይገባል መዝሙር ፷፰· ፬፡ ፺፭፡ ፱ ፡

ለ. ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ ጫማ አውልቆ ወገብን ታጥቆ አደግድጎ መግባት ነው ጫማ አድርጎ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት ክልክልነው፤ ዘፀ· ፫፡፭-፯ የሐ፡ ሥራ፯፡፴፫፡ ፍት· ነገ · ፲፪)።

ሐ. አሳብን በመንፈሳዊ ነገር ወስኖ ወደ ውጭ ወደ ዓለማዊ ነገር እንዳይሔድ መግታትና መቈጣጠር ያስፈልጋል ።

መ. ከካህን ቀርቦ መስቀል መሳለምና በረከትም መቀበል ያሻል ።

ሠ. በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ተሥለው የሚገኙትን የሥላሴን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የእመቤታችንን የቅድስት ድንግል ማርያምን የመላእክትን የነቢያትን የሐዋርያትን የጻድቃን የሰማዕታትን የደጋጎች ቅዱሳን አበውን ሥዕሎች እጅ መንሣትና የአክብሮት ስግደት መስገድ ይገባል ።

ረ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሳቅ ስለ ዓለማዊ ሥራ መነጋገር ክልክል ነው ፡ ከገቡ በኋላ ዝምታ ጸጥታ ፍርሃት የእግዚአብሔርን ምሕረት በጥብዓተ ልብ መፈለግ አለ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን የመዘምራንን ማኅሌት የቅዱ

www.ethiopianorthodox.org

ሳን መላእክትን ምስጋና የነቢያትን ትንቢት የሐዋርያትን ስብከት መስሚያና የልዑል እግዚአብሔርን ነገር መማሪያ ቦታ ስለሆነች ነው። ከዚህም ሌላ የሥጋ ወደሙ ምሥጢር የሚፈጸምባት ናት ( ዘሌዋ. ፳፮ ፡ ፪ ። ዮሐ፡ አፈ. አን ፡ ፲፱-፴፪። «እስመ ቤተ ክርስቲያን በአምሳለ ሰማይ ወመሃይምናን ይኩኑ ውስቴታ አምሳለ መላእክት ወያጽምዑ በትዕግሥት ወበአርምሞ ወይትማሐለሉ በልቦሙ ዘእንበለ ዕረፍት» ዮሐ፡ አፈ ፡ አን፡ ፴፰ «ኢይትናገር አሐዱ ለግሙራ በውስተ ቤተ ክርስቲያን እስመ ቤተ እግዚአብሔር ፥ ቤተ ጸሎት ወአኮ ቤተ ነገር ወዘተናገረ በውስቴታ ይፃዕ ወኢይቅረብ በይእቲ ዕለት» ቀኖና አቡሊዲስ አን ፡ ፲፯)

«ወሶበ ትቀውም ቅድመ ንጉሥ ምድራዊ ዘኢትደፍር ከመ ትስሓቅ ወኢምንተኒ ትስሕቅኑ ሶበ ትቀውም ቅድመ ንጉሠ ነገሥት ሰማያዊ» ዮሐ ፡ አፈ ፡ አን ፡ ፯) ።

«እመኬ ዓለማዊ ሶበ ይስሕቅ በውስተ ቅዳሴ ያውጽዕዎ አፍአ ወኢይመጥውዎ እምሥጢር ቅዱስ» (ቀኖና ፡ ባስ ፡ አን ፡ ፹፱) ።

ሰ. አጭርና ያደፈ ልብስ ለብሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ክልክል ነው ፤ ረዘም ያለና ንጹሕ ልብስ ለብሶ መሄድ ያስፈልጋል (ዘፀ ፡ ፲፱ ፡ ፲-፲፭)፲፩፤ በተለይ ሴቶች ራሳቸውን ተከናንበው እንዲጸልዩ ታዝዞአል ።
«አይባእ ብእሲ ኀበ ቤተ ክርስቲያን ወኢይጸሊ ውስቴታ ዘእንበለ ይኩን ልብሱ ድርማንቀ



በከመ ይቤ ጳውሎስ ሐዋርያ ለብሔረ ቆሮንቶስ ቀዳማዊ ለእመ ኮነ ዘይጼሊ አልባሲሁ ሐጺረ ወይትከሠት እምኔሁ ጊዜ ስግደቱ ይእቲ መጸዓሉ ዘቀበጽነ በእንቲአሁ ወይከውን ጌጋየ ለዘነጸሮ ወለዘተነጸረ እስመ ለዘነጸረ ይመጽእ ቦቱ ሰሐቅ ወበእንተዝ ይወርድ ላእሌሁ ከመ ወረደ ላዕለ ወልደ ኖኅ ሶበ ሰሐቀ ዲበ አቡሁ በከመ ይቤ መጽሐፈ ኦሪት ወዘነጸረ እስመ ኮነ ምክንያተ ለአብጽሖ ጌጋዩ ለዘነጸረ አበሳሁ (ዮሐ . አፈ. ፡ አን ፡ ፩፡ ፱. ፵፱ ፡ ፹፪ ። ኦሪ፡ ዘፍ፡ ፱ ፡ ፳፩—፳፯ ። ፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፩ ፡ ፫-፲፩) ።

ቀ. ወደ ቤተ ክርስቲያን ባዶ እጅ መሄድ አይገባም መባዕ ፥ ምጽዋት ይዞ መሄድ አለ ዘፀ ፡ ፴፬ ፡ ፳

## ካህናትና ምእመናን ለጸሎት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሔዱባቸው ጊዜያት

የጸሎት ጊዜያት ፯ ናቸው መዝ፡ ፩፻፲፰ ፡ ፩፻፷፬፡ እነዚህም፥

ሀ. ነግሀ (ከጥዋቱ ፲፪ ሰዓት)
ለ. ሠለስቱ ሰዓት (ከጥዋቱ ፫ ሰዓት)
ሐ. ስድስቱ ሰዓት (ዕኩለ ቀን)
መ. ተሰዓቱ ሰዓት (ከቀኑ ፱ ሰዓት)
ሠ. ሠርክ (ከቀኑ በ፲፩ ሰዓት)
ረ. ንዋም ( ከማታው በ፫ ሰዓት)
ሰ. መንፈቀ ሌሊት (ዕኩለ ሌሊት ) ናቸው
ቀ. ከ፯ቱ ጊዜያት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔደው የሚጸልዩባቸው ነግህና ሠርክ ናቸው ፤ በቀሩት

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜያት ግን በያሉበት ሊጸልዩ ይገባል (ፍት፡ ነገ አን ፲፬ ረስጣ ፶፰ ፡ ፶፯ ፡ ድስቅ ፡ ፲፪) ።

## የጸሎት ሥርዓት

የጸሎት ሥርዓት በብዙ ወገን ይከፈላል ።

ሀ. የግል ጸሎት ማቴ ፡ ፮ ፡ ፭—፲፫

ለ. የቤተ ሰብእ ጸሎት የሐ ፡ ሥ፡ ፲ ፡ ፩—፱

ሐ. የማኅበር ጸሎት የሐ ፡ ሥ፡ ፩ ፡ ፲፬ ፡ ፳፭ ። ፫ ፡ ፩ ፡

መ. የባሕታውያን ጸሎት ፍት ነገ ፲፬

ሠ. ልዩ የካህናት ጸሎት (ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፲፬)

## የጸሎት አፈጻጸም ።

በጸሎት ጊዜ

ሀ. ዓምድ ግድግዳ ሳይደገፍ መቋሚያ ሳይዝ በሁለት እግር ቀጥ ብሎ መቆም ነው ፤

ለ. ወገብን በዝናር መታጠቅ ልብስን ዝቅ አድርጎ ማደግደግ ነው ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፲፬ ፡

ሐ. በጸሎት ጊዜ ፊትን ወደ ምሥራቅ መልሶ መቆም ወዲያና ወዲህ ወደ ግራ ወደ ቀኝ ወደ ሌላም አለማለት ።

መ. ጸሎት ሲጀመርና ሲፈጸም አመልካች ጣትን ከሌሎች ጣቶች ጋር አመሳቅሎ በትእምርተ መስቀል አምሳል በጣት ማማተብ ነው ፤ ሲያማትቡም ከላይ ወደታች ከግራ ወደ ቀኝ በማድረግ ነው ፤ በማማተብ ጊዜ የክርስቶስን መከራ መስቀል ማሰብ ያስፈልጋል ።

ሠ. የሚጸልይ ሰው በትሕትናና በጸጥታ ሁኖ ለሌላ ሰው እንዳይሰማ ለራሱ ጆሮ ብቻ እንዲሰማ አድርጎ መጸለይና ደረቱን መድቃት ይገባዋል ይህንም የሚያደርገው ስለአለፈው ኃጢአቱና በደሉ ነው ። ፩፡ ሳሙ ፩፡ ፲፫ ።



ረ. የሚጸልይ ሰው በኀቡዕ ልብ በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገራል አሳቡን በእግዚአብሔር ላይ ይጥላል የዓለምን አሳብ ሁሉ ይተዋል ፤

ሰ. የሚጸልይ ሰው ሲያማትብ«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አአትብ ገጽየ ወኵለንታየ በትእምርተ መስቀል»እያለ ነው ፤ ሁለተኛም«እግዚኦ መሐረነ እግዚኦ መሐከነ እግዚኦ ተሣሃለነ ወባርከነ አሜን» እያለ ያማትባል ሦስተኛም ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን አእግዚኦ ረሰየነ ድልዋነ ከመ ንበል በአኰቴት አቡነ ዘበሰማያት «የሚለውን ጸሎት ፫ ጊዜ እየደገመና እየሰገደ በማማተብ በመስገድ በጸሎት መጀመሪያና መጨረሻ ጊዜ ማድረግ አለበት ።

ቀ. የጸሎቱ ቅደም ተከተል መጀመሪያ አቡነ ዘበሰማያት ሁለተኛ መዝሙረ ዳዊት ቀጥሎ አቡነ ዘበሰማያት ጸሎተ ሃይማኖት በመጨረሻ ኪርያላይሶን ፵፩ ጊዜ ይደግማል ይህንን ጸሎት ማንኛውም ክርስቲያን መጸለይ አለበት ይህንን የማያውቅ ምእመን ከካህናት ተምሮ መጸለይ ግዴታው ነው ካህናት ግን ቅዱሳት መጻሕፍትን ሁሉ ተምረው እንዲጸልዩ ታዝዘዋል ኤፌ ፡ ፮ ፡ ፲፱-፳ ማቴ ፡ ፯ ፡ ፱-፲፫) ።

www.ethiopianorthodox.org

በ. ሲጸልይ ማልቀስ ደረቱን መድቃት ይገባዋል ፤ ሲያለቅስም እያንዳንዱን በደሉንና ኃጢአቱን እያሰበ በየአንዳንዱ በደል ዕንባ ማፍሰስ ነው ።

ተ. የሚጸልይ ሰው በጸሎት ላይ ሳለ ጸሎቱን አቋርጦ ከማንም ሰው ጋር ፈጽሞ መነጋገር የለበትም ጸሎቱን እስከ ሚጨርስ ድረስ ቃል መለዋወጥና ማንንም ወደርሱ መጥቀስ አይገባውም ጸሎቱን የሚያቋርጥ ችግር ቢገጥመው ግን በአቡነ ዘበሰማያት አሥሮ ንግግሩን ሲፈጽም ከአቋረጠበት ጀምሮ ጸሎቱን ሊጸልይ ይገባል ።

ከዚህ ቀደም ብለን ከሀ—ሰ በስም የተጠቀሱት ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያን በዝርዝር ይቀርባሉ ።

## ምሥጢረ ጥምቀት

ስለ ሥርዓተ ጥምቀት ከመጻፍ አስቀድሞ የጥምቀት አመሠራረትና አመጣጥ እንዴት እንደሆነ የጥምቀት ምሥጢርና ዓላማ ምን እንደሆነ ማወቅ ስለሚያስፈልግ ይህንኑ በቅድሚያ መግለጽ ያሻል ።

## የጥምቀት አመሠራረት

ጥምቀት በወንጌል የታዘዘ ከእግዚአብሔር የምንወለድበት ነው ።

ሌሎችንም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለመሳተፍ የሚቻለው ከጥምቀት በኋላ ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ በ፴ ዓመቱ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ ። ስለጥ



ምቀቱም ቀደም ብሎ በብሉይ ኪዳን የተነገረ ትንቢትና የተመሰለ ምሳሌ አለ (መዝ፡፷፯ ፡ ፳፱።፳፰፡፫ ። ፸፯ ፡ ፲፯ ። ፱፲፫ ፡ ፩-፯ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፪ ፡ የሐ፡ ሥ. ፩ ፡ ፰ ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው በጥምቀቱ ጥምቀታችንን ሊቀድስልን ነው ።

የመድኃኒታችን ጥምቀት አይሁድ እንደሚያደርጉት የማንጻት ልማድ ወይም ኃጥአን መጸብሐን ከዮሐንስ እንደተጠመቁት ጥምቀት አልነበረም ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠምቆ ከውኃው ከወጣ በኋላ «አብ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ» ብሎ የባሕርይ ልጅነቱን መስክሮለታል ፤ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀምጧል ማቴ ፫፡ ፲፮—፲፯ ። በትምህርቱ መጨረሻ «በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ» በማለት ጥምቀትን አዝዞአል ። ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱)

## ከመጠመቅ በፊት የሚያስፈልጉ ነገሮች

ሀ/ ከጥምቀት በፊት ፩ኛ. ትምህርት
፪ኛ. እምነት ያስፈልጋል ተጠ

ማቂው በዕድሜ ከፍ ያለ ከሆነ የክርስትናን ትምህርት የተማረ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ መሆን አለበት ጌታችን «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ብሎ አልና ማር ፡ ፲፮ ፡ ፲፮ ።

እምነት መሠረት ነው ሌሎች ምግባራት ግን ሕንጻዎች ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፩. ለቍርባን የሚደረግ ጥንቃቄ

ሀ. የሚቀድሱና የሚቈርቡ ሰዎች በጋብቻ ሥርዓት የሚኖሩ ከሆኑ ከመቀደሳቸውና ከመቍረባቸው በፊት ፫ ቀን ፡ ከቍርባን በኋላ ፪ ቀን ከሩካቤ መከልከል ይገባቸዋል ።

ለ. ቍርባን መቀበል ንስሓ ገብቶ ከኃጢአት ነጽቶ ነው ከክርስቲያን ወገን ማንም ሰው የክርስቶስን ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ትንሣኤ ዘለሕይወትን ሊወርስ ቢወድ ልቡን ከቂም ከበቀል ሰውነቱን ከበደል ንጹሕ አድርጎ መቀበል አለበት ይህም ማለት ሰው ስለሚያውቀው ኃጢአት ተናዞ ስለማያውቀው ይቅር በለኝ እያለ በንጹሕ ይቍረብ ማለት ነው ከኃጢአት ሳይነጻ ቢቀበል ግን የጌታ ሥጋ እንደሆነ አላወቀምና እንደ ምድራዊ ምግብም አቃሎታልና በኃጢአት ሳለ ያለ ኃፍረት በድፍረት ሥጋውን ደሙን በመቀበሉ ሥላሴ ይፈርዱበታል ፩ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫-፳፱ ።

ሐ. ሥጋ ወደሙ ለመቀበል ፲፰ ሰዓት ከእህል ከውሀ ተከልክሎ መጾም ይገባል ፤

ማስረጃ«ወኢይንሣእ መኑሂ ቍርባነ ዘእንበለ ይጹም በንጹሕ» (ፍት ፡ ነገ ፡ ፲፫ ፤ ረስጠብ ፵፮ ጴጥ፥

መ. ሰው ዝንየት (ርስሐት ) ካገኘው በዚያ ቀን አይቈርብም ።

ሠ. ካህን በሚቀድስበት ቀን ዕንቅፋት ቢያገኘው ማለት ነስር ትውኪያ ብስና ማንኛውም የአካል



መድማት መቁሰል ወደ አፍ የሚገባ እንደ ትንኝ ዝምብ ይህን የመሰለ ሁሉ ቢያጋጥመው በዚያው ዕለት መቀደስ መቍረብ አይገባውም ።

ከቍርባንም በኋላ ከአለመጠንቀቅ የተነሣ እንዲህ ያለ ነገር ቢያጋጥመው ንስሐ ሊሰጠው ይገባል ፤ ንስሐውን ሳይፈጽም እንደገና መቍረብ አይችልም ይህም ለካህን ብቻ ሳይሆን ምእመናንንም ሁሉ የሚመለከት ነው ።

ማስረጃ/ ያዕቆብ ዘእልበረዳኢ

## ፪. በጸሎትና በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ ካህናትና ምእመናን የሚቆሙበት ቦታ

ሀ. በቤተ ክርስቲያን ሁሉም በየማዕርጉ ይቆማል ፤ ይኸውም ኤጲስ ቆጶሳት (ሠራዕያን) እንደ መሆናቸው በታቦቱ ፊት ይቆማሉ፤ቀሳውስት መምህራን እንደመሆናቸው ከኤጲስ ቆጶሳት ቀጥለው ይቆማሉ፤ሊቀ ዲያቆናት ከኤጲስ ቆጶሱ አጠገብ ይቆማል፤ዲያቆናት ተላላኪዎች እንደ መሆናቸው ከቀሳውስት ቀጥለው ይቆማሉ ።

ከዲያቆናት ቀጥለው ሕዝቡ ይቆማሉ ቦታው ከበቃ ሕፃናት በአንድ ወገን ይቆማሉ ቦታ ከጠበበ ሕፃናት ከአባቶቻቸው ተጠግተው ይቆማሉ ።

ወንዶች በአንድ ወገን ሴቶች በአንድ ወገን ይቆማሉ ቦታ ካለ ሕፃናት ሴቶች በአንድ ወገን ይቆማሉ ቦታ ከጠበበ ግን ከእናቶቻቸው ተጠግተው ይቆማሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

ደናግል ሴቶች ባልቴቶች የቀሳውስት ሚስቶች ግን ከሌሎች ሴቶች በላይ ይቆማሉ፤ሥጋውን ደሙን በፊት ይቀበላሉ (ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፲፪) ፡ ተመልከት

ለ/ ካህናትና ምእመናን በታዘዘላቸው ቦታ እንዲቆሙ ዲያቆናት ያስተናብራሉ «ወይኩኑ ዲያቆናት ዘያስተሐምሙ ከመ ይባዕ ለለ አሐዱ አሐዱ ውስተ መካን ዘሥሩዕ ሎቱ» እንዳለ ፍት ፡ ነገ አንቀጽ ፲፪ ድስቅ ፲፪ ኒቅያ ፳፩ ።

## ካህኑ ለቅዳሴ ሲገባ ።

ካህኑ ልብሰ ተክህኖ ከመልበሱ በፊት አብሮት የሚቀድስ ዲያቆን መኖሩን ማረጋገጥ አለበት ። ካህን ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ በታቦቱ ፊት ከመጋረጃ ውጭ አንድ ጊዜ ፡ በመጋረጃ ውስጥ በመሠውያው ፊት ሦስት ጊዜ ይሰግዳል ።

መ. ካህን በክብር በፍርሐት ሁኖ «ተንሥኡ ጸልዩ» እያለ ለሕዝቡ የሚሰብክለት ዐዋጅ የሚናገርለት ዲያቆን ሳይዝ እንዳይቀድስ ተከልክሉዋል ። ዲያቆኑም አሰምቶ የሚያነብና የሚያዜም ሊሆን ይገባል ።

ሠ. ሕዝቡ ሳይሰበሰቡ ቅዳሴ መግባት ክልክል ነው ፍት ፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፲፪ ። በስ ፺፺

## መቀደሻ አልባሳት

ረ. የሚቀደስባቸው አልባሳት በቤተ ክርስቲያን ዕቃ ቤት ሊቀመጡና በንጽሕና ሊጠበቁ ይገባል ከዚህ ውጭ በሌላ ቦታ እንዲቀመጡ አልተፈቀደም (ሕዝ ፡ ፵፬ ፡ ፲፱ ። ፍት ፡ ነገ ፡፲፪)



ሰ. ካህናት የሚደርቡት ካባ ላንቃ ፩ መንዲል (ከልጅ) ያለው እንዲሆን ታዝዟል መንዲል ወይም ከልጅ ማለት ለምድ ነው ።

ቀ. ካህናት በቀደሱ ጊዜ የሚለብሱት እስከ ተረከዛቸው የሚደርስ መሆን አለበት (ፍትነገ፡፲፪)።

በ. ካህኑ ልብሰ ተክህኖ ከመልበሱ በፊት ልኩ የሚሆነውን መርጦ ይለብሳል ፤ ልብሰ ተክህኖ ከለበሰ በኋላ ማውለቅ አይገባውም ቀሚሱ ከረዘመበት በዝናር ይታጠቀዋል (ፍት ፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፲፪) ።

ተ. የሚቀድሱ ካህናት ሲቀድሱ ነጭ ልብስ እንዲለብሱ ታዝዟል የሚቈርቡ ምእመናንም ንጹሕ ነጭ ልብስ ለብሰው መቅረብ ይገባቸዋል ። «ወአልባሰ ቅዳሴ እለይቄድሱ ቦቶን ይኩና ጸዐድወ በከመ ይደሉ ለካህናት ወአኮ ኅብራት» እንዲል ፍት. ፡ ነገ ፡ ፲፪ ፡ በዶስ ፡ ፴፯ ፡ በስ ፺፯ ።

ኀ. ካህኑ ልብሰ ተክህኖ ከመልበሱ በፊት ጳጳስ ካለ ጳጳሱን አስባርኮ ይለብሳል ከሌለ ራሱ ባርኮ ይለብሳል ።

ነ. ሕዝቡ እንዳያንቀላፉ እንዳይፈዙ ዲያቆኑ ያነቃቸዋል (ፍት ፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፪ ። ድስቅ ፡፲፪)

አ. ካህኑ ቅዳሴ ሲገባ ከሁሉ አስቀድሞ አንድ ጊዜ ከታቦቱ ፊት ሰግዶ አንድ ጊዜ ቀሳውስቱን አንድ ጊዜ ዲያቆናቱን እጅ ይነሣል ።

www.ethiopianorthodox.org

ከ. የሚለብሰውን ልብሰ ተክህኖ ይዞ ፊቱን ወደ ምሥራቅ መልሶ ፫ ጊዜ ሰግዶ አቡነ ዘበሰማያ ትን ይደግማል ።

## ለመሥዋዕት የሚገባ ስንዴ

ወ. መሥዋዕት የሚሆነው በወራቱ የደረሰ ዋግ ያል መታው እንክርዳድ የሌለበት ንጹሕ ስንዴ ነው (ፍት፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፫ ፤ ረስጠ፳ ፡ ፫)

ዐ. ለመሥዋዕት የሚቀርበው ኅብስት ዕለቱን የተ ሠራ እንዲሆን ታዝዟል ኮተውዋም በኋላ ለማ ግስቱ አያድርም (ፍት፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፫ ፡ ረስጣ ፡ ፴)

ዘ. ኅብስቱም ነቅዕ ያለበት አይሆንም ነቅዕ የሌ ለበት ያላረረ ያልጠቈረ እንዲሆን ታዝዘዋል ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፲፫ ፡ በስ ፡ ፺፰ ።

የ. ኅብስተ አኰቴቱ ገና ሲሠራ ሥርዓቱ አሥራ ሦስት መስቀል ባለው ማኅተም ታትሞ ይሠ ራል ።

## ለመሥዋዕት የሚገባ ወይን

ደ. ወፍ ያልመጠጠው አይጥ ያልቈረጠመጠው መጀ መሪያ የደረሰው ወይን ሲሆን ይገባል ።

ገ. ለመሥዋዕቱ የሚቀርበው ወይን በእሳት ከሚ በስሉ ከጠጅ ከዐረቄ ወገን በማንኛውም አይሠ ራም ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፲፫ ፡ ረስጣ ፡ ፫ ።



ወይኑንም ሲሠሩ ጥሩ መሆኑን ተመልክቶ መሥራት ይገባል ፤ ንጹሕ ጽሩይ ከአልሆነ ለመሥዋዕት አይገባም ፤ ከሚሶ የበለጠ ውኀም አይጨመርበትም (ፍት ፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፫ ። በስ ፡ ፺፱) ወይኑም ዓመት ያለፈውና መዓዛው የለወጠ ለመሥዋዕት ሊቀርብ አይገ ባም ፍት ፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፫ ፡ በስ፡ ፩፻፪ ።

## አግብኦተ ግብር (ከቤተ ልሔም ወደ ቤተ መቅደስ)

ዲያቆን በቤተ ልሔም ኅብስቱንና ወይኑን ለመሥዋዕት ከሠራና ከአዘጋጀ በኋላ ንፍቁ ዲያቆን ኅብስቱን በመሶበ ወርቅ በራሱ ላይ አድርጎ፡ ወይኑን ሠራዒው ዲያቆን በጽዋዕ ይዞ ቃጭል እያቃጨለ በፊት በፊቱ ፤ ንፍቁ ቄስ መስቀልና ማዕጠንት ይዞ እያጠነ በኋላ በኋላው ሆነው ከቤተ ልሔም ወደ ቤተ መቅደስ ይገባሉ ። ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፲፪ ። ረስጠብ፡፺፪

እሑድ እሑድ አራት ኅብስት ይገባል ዘወትር ግን ሦስት ሦስት ይገባል ።

ደሙ በምድር ላይ እንዳይፈስ ጽዋውን ከመጠን በላይ መሙላት አይገባም ሲያቀብልም መ ጠንቀቅ ይገበዋል( ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፲፫ረስጣ ፵፭)።

## ሥርዓት ዘጊዜ ቅዳሴ

ሀ. ቀዳስያን መንበሩን ከበው ይቆማሉ ሠራዒ ቄስ ፊቱን ወደ ምሥራቅ አድርጎ በምዕራብ ይቆማል ፤ ሠራዒ ዲያቆን ፊቱን ወደ ምዕራብ አድርጎ በምሥራቅ ይቆማል ንፍቅ ቄስ ፊቱን ወደ ሰሜን አድርጎ በደቡብ ይቆማል ፤ ንፍቅ ዲያቆን ፊቱን ወደ ደቡብ አድርጎ በሰ

www.ethiopianorthodox.org

ሜን ይቆማል ፤ ሦስተኛው ቄስ በስተግራው ቆሞ ለሠራዒው ቄስ መብራት ያበራለታል መጽሐፍ ይገልጥለታል ።

ሦስተኛ ሆኖ የሚገባ ቄስ ባይኖር ዲያቆን መብራት ያበራል መጽሐፍ ይገልጣል ይህን ሲሠራ ግን ዲያቆን መንበሩን እንዳይጠጋ እንዳይዳስስ መጠንቀቅ ይገበዋል ።

ለ. ዲያቆናት በዓውደ መንበሩ ቆመው ተሰጠውን ይቀበላሉ ፤ በተለይ ፪ ዲያቆናት ከልዝብ ሐር የተሠራ መነሳንስ ይዘው አንዱ በቀኝ አንዱ በግራ ቁመው ወደ ጽዋው ምንም ምን እንዳይ ገባ ተሐዋስያንን ይከለክላሉ (ፍት ነገ ፡ አን፡ ፲፱ ፡ ረስጣ ፶፪) ።

ሐ. የሚቀድሱ ካህናት በቅዳሴ ጊዜ የጌታን ነገረ መስቀል በማሰብ በቅድመ እግዚአብሔር መቆማቸውን ባለመዘንጋት ይቀድሱ እንጂ ዜማውን ከልክ አሳልፈው በማቀማጠል ማዜም አይገባቸውም (ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፲፱ ፡ በስ ፡፺፱)

መ. የሚቀድሰው ካህን በሥጋዬ ይቀስፈኛል በነፍሴ ይፈርድብኛል ብሎ ፈርቶ መቆም ይገባዋል ፤

ሠ. በቤተ ክርስቲያን የተሰበሰቡ ምእመናን ሁሉ የእግዚአብሔርን ነገር (ትምህርቱን ጸሎቱን) ለመስማት በጸጥታ መቆም አለባቸው ፤ ተሰጥዎ ከመቀበል በቀር መናገር መሳቅ አይገባቸውም በቅዳሴ ጊዜ ፈጽሞ ፡ የሚስቅ አይኑር (ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፲፪ ፡ ድስቅ ፲፪ ፤ ኒቅያ ፳፩፤ በስ ፸፪) ።



ረ. ካህናት በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ ጥምጥማቸውን ማውለቅ ቀጸላቸውን ማውረድ ወንጌልና ኪዳን ሲነበብ አክሊላቸውን ማውረድ አለባቸው ፤ በሌላ ጸሎት ጊዜ ካህናት ጥምጥማቸውን ማውለቅ አክሊላቸውን ማውረድ ቢያቅታቸውም ወንጌል ሲነበብ ይህን መፈጸም አለ ፤ ወንጌል ሲነበብ ማድረግ ባይቻልም በሚሳለሙበት ጊዜ ራስን መግለጥ ግዴታ ነው ።

ሰ. ወንጌል ሲነበብ መቆም ነው እንጂ መቀመጥ ክልክል ነው ።

ቀ. ወንጌል ሲሳለሙም «ነአምን በቃለ ወንጌል ቅዱስ» እያሉ ነው ።

በ. ወንጌል ከተነበበ በኋላ ኤጲስ ቆጶስ ካለ ወንጌሉን በእጁ ይዞ በክፍሎቹ የተነበበውን ለሕዝቡ ተርጕሞ መንገር ይገባዋል ፤ ኤጲስ ቆጶስ ከሌለ ትርጓሜውን የሚችል ካህን እንዲያስተምር ታዝዞዋል። (ፍት፡ ነገ፡ ፲፱፡ በደስ፡ ፺፱)

ተ. ኤጲስ ቆጶሱ ወይም ቄሱ ወንጌልን ከማንበቡ በፊት ንፍቅ ቄስ «ርሑቀ መዓት» የሚለውን ጸሎት ይጸልያል (ሥር ፡ ቅዳ ፡ ተመልከት) ።

ኀ. ካህኑ በሥርዓተ ቅዳሴ መጀመሪያና በፍሬ ቅዳሴ መጀመሪያ ፪ ጊዜ እጁን ይታጠባል እንዲሁም ሌሎች ካህናትና ዲያቆናት ከቍርባን አስቀድሞ እጃቸውን ይታጠባሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

ነ. በቅዳሴ ጊዜ በሁለት ጧፍ እንጂ በአንድ ጧፍ አይቀደስም ።

አ. ካህኑ በቅዳሴ ጊዜ ሙቀት ሳይለየው ሥጋውን ደሙን ለማቀበል ይችል ዘንድ የነቃ የተጋ መሆን አለበት ።

ከ. በቅዳሴ ጊዜ ዕርገተ ዕጣን አይቀርም የሚደረገውም ዕርገተ ዕጣን አምስት ጊዜ ነው

ወ. ማዕጠንት (ጥና) የሚይዝና የሚያጥን ቄስ ነው እንጂ ዲያቆን በእጁ ጥና ይዞ አያጥንም ኤጲስ ቆጶስ መሥዋዕቱን ካጠነ በኋላ ሕዝቡና ካህናቱን ቤተ ክርስቲያኑን እየዞረ እንዲያጥን ጥናውን ለቄስ ይሰጣል (ድስቅ ፲፪ ፡ ፳፫ · ፴፰)

ዐ. የቅዳሴ ቡራኬያት ፵፪ ናቸው እነዚህም ፳፩ የአፍአ ፳፩ የውስጥ ቡራኬያት ናቸው ፤ የአፍአ ቡራኬ ለካህናትና ለሕዝብ ነው የውስጥ ቡራኬ ግን በሥጋ ወደሙ ላይ ነው የአፍአ ቡራኬ በመስቀል ነው የውስጥ ቡራኬ ግን ካህኑ በእጁ ይባርካል፤ ንፍቅ ካህን ግን አይባርክም ሠራዒው ካህን ሥጋ ወደሙን በእጁ እንጂ በመስቀል አይባርክም ጽዋውንም ሲባርክ የጽዋውን ከንፈር በግራ እጁ መያዝ አይገባውም በቀኝ እጁ በትእምርተ መስቀል አምሳል መወዝወዝ አለበት ።

ዘ. በቅዳሴ ጊዜ የሠራዒው ካህን ዑደት ፯ ነው ፤ ይኸውም በመጀመሪያው ጸሎተ ዕጣን በመቅደሱ ውስጥ ፫ ፤ በአንቀጸ ምዕራብ «ስብሐት



ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ» እያለ አጥኖ ከፈጸመ በኋላ «እግዚአብሔር አምላክነ በከመ አንሐልከ ቅድመ ጥቅማ ለኢያሪኮ» እያለ ሲዞር አንድ ፤ በሁለተኛው ጸሎተ ዕጣን ፫ በድምሩ ፯ ዑደት ይሆናል ። ትርጒሙ ኢያሱ ወልደ ነዌ የኢያሪኮን ግንብ ፯ ቀን ዞሮ እንዳፈረሰ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ፯ቱ ጊዜያት በተቀበለው መከራ የሰውን ኃጢአት ማጥፋቱን ለማሰብና ለማሳሰብ ነው ።

የ. የንፍቅ ካህን ዑደት ፫ ነው ግብረ ሐዋርያት አንብቦ ሲገባ አንድ ጊዜ፣ ወንጌል ተነብቦ ሲገባ አንድ ጊዜ፣ሠራዊተ መላእክቲሁ ተብሎ ሲገባ አንድ ጊዜ ይዞራል በድምሩ ፫ ይሆናል ።

ደ. እማሬያት ፲፩ ናቸው እነዚህም በጸሎተ እንፎራ ፪ «አዕ ፦ ተ» ሲል በሥጋው አንድ በደሙ አንድ «ይረስዮ» ሲል ሁለት ሥጋ ቅዱስ ሲል አንድ ደም ክቡር ሲል አንድ «እስመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ ሲል» አንድ በመጀመሪያው «አአምን» አንድ ፤ በመጨረሻው አአምን አንድ ፲፩ ይሆናል ።

ገ. ጸሎተ ቅዳሴ ከተጀመረ በኋላ ዲያቆን «እትዉ በሰላም» ብሎ ሳያሰናብት በከባድ ችግርና በሕመም ካልሆነ በስተቀር ከቤተ ክርስቲያን መውጣት ክልክል ነው (ፍት ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፲፪፣ በስ ፶፪) ።

www.ethiopianorthodox.org

ጠ. ዲያቆን «ጸልዩ በእንተ ሰላም»ብሎ ስለ ሰላም እንዲጸለይ በቅዳሴ ላይ ትእዛዝ ሲሰጥ ወንዶች ወንዶችን ሴቶች ሴቶችን ሁሉም በየጾታቸው እጅ ይነሣሣሉ ወንዶች ሴቶችን ሴቶች ወንዶችን እጅ አይነሡም (ፍት ፡ ነገ አንቀጽ ፲፪ ፡ ረስጣ ፩፻፫ ፡ ፴፪ ፡ ፶፫ ።)

ጸ. ካህኑ ኅብስቱን ሲፈትት ከላይ ወደ ታች ከቀኝ ወደግራ ከግራ ወደ ቀኝ ከታች ወደ ላይ በትክክል መስቀሉን ተከትሎ ይፈትተዋል ሲፈትትም እንዳይነጥበው መጠንቀቅ አለበት (ፍት ፡ ነገ ፡ አን ቀጽ ፲፪ ፡ በስ ፡ ፺፱) ።

## ፱. ለመቍረብ የሚያበቃና የማያበቃ ሁኔታ

ሀ. ቅዳሴ ሲጀመር ያልነበረ ሰው አይቈርብም ፤ ቅዳሴ ሲጀመር ያልነበረ ካህንም እንደዚሁ ሥጋ ወደሙ ሊቀበል ሊያቀብል አልተፈቀደለትም (ፍት ፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፲፪ ፡ በስ ፡ ፺፯ ።)

ለ. ከምእመናን በስተቀር ያላመኑ ሰዎች ሥጋ ወደሙ እንዳይቀበሉ መጠበቅና መቈጣጠር ያስፈልጋል ፍት ፡ ነገ ፡ ፲፫ ፡ ረስጠብ ፡ ፴፬ ።

ሐ. በንስሓ የተለየሰው የንስሓ ጊዜውን ሳይፈጽም ለሞት የሚያበቃ ደዌ ቢታመም ሥጋ ወደሙ ከመቀበል አይከለከልም ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ከዳነም ከምእመናን ጋር በጸሎት ይሳተፋል በቀኖና ወደተለዩ ሰዎች አይመለስም (ፍት ፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፫ ፡ ዕንቆራ. ፲፭) ።



መ. ጋኔን የሚጥለው ሕመም ያለበት ፡ ሰውን የማይ ሰድብ ከጣለው በኋላ ዐረፋ የማያስደፍቀው ከሆነ ሥጋ ወደሙ ከመቀበል አይከለከልም (ፍት ነገ ፡ ፲፫ ፡ ጢሞ) ።

ሠ. ሥጋውን ቄሱ በእጁ ሲያቀብል ደሙን ንፍቅ ቄስ በዕርፈ መስቀል ለካህናት ፡ ዲያቆን ለምእመናን በዕርፈ መስቀል ይሰጣል እንጂ ንፍቅ ቄስና ዲያቆን ሥጋውን ደሙን በእጃቸው አይነኩም ።

ረ. ያቈራረቡ ተራ ቀጥሎ እንደተዘረዘረው ነው፤

፩. ሊቀ ጳጳሳት ይቀበላሉ
፪. ጳጳሳት
፫. ኤጲስ ቆጶሳት
፬. ቆሞሳት
፭. ቀሳውስት
፮. ዲያቆናት
፯. ንፍቀ ዲያቆናት በየተራቸው ይቈርባሉ ከነሱም ቀጥሎ ሁሉም በየማዕርጉ ተራ ይቈርባል ከካህናት ቀጥሎ በዕለቱ ክርስትና የተነሡ ይቀበላሉ ፤ ከዚያም ሕፃናት ቀጥሎ ደናግል ከዚያም ሕዝባውያን ምእመናን ሥርዓተ ቅዳሴው እንደሚያዝዘው በየማዕርጋቸውይቈርባሉ።

ሰ. ቍርባን ተቀብሎ ማየ መቍረር ይሰጣል (ፍት፡ ነገ አን ፲፫ ፡ ክርስጣ ፳፭) ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## ፩. ከቍርባን በኋላ የሚደረግ ጥንቃቄ

ሀ. ከቈረቡ በኋላ በዚያው ዕለት ወደ ፍርድ ቤት መሄድና መሟገት ክልክል ነው ።

ለ. በቈረቡበት ቀን ከሚስት መገናኘት ፣ አብዝቶ መብላት መጠጣት ጥፍር መቍረጥ ጠጕር መላጨት በውኃ መታጠብ ከልብስ መራቈት ክልክል ነው ፤ (ሥርዓተ ቅዳሴ ቍጥር ፩፻፳፮) ።

## ካህኑ ሥርዓተ ቅዳሴን ለመፈጸም የሚያደርገው

## የመግቢያ ጸሎት

## ክፍል አንድ

ሀ. ካህኑ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ መዝሙረ ዳዊት ፺ኛውን መዝሙርና አቡነ ዘበሰማያትን ይደግማል ።

ለ. ለዲያቆኑ አንድ ጊዜ እማኄ ያደርጋል ።

ሐ. ካህናቱ « እገኒ ለከ እግዚእ በኵሉ ልብየ ወእሰግድ ውስተ ጽርሐ መቅደስከ በፈሪሆትከ» እስከሚለው ድረስ እያነበቡ ይመልሳሉ ።

መ. ከዚህ በኋላ ካህኑ ወደ መንበሩ ተጠግቶ ታቦቱን በመዳሰስ ጳጳስ ካለ ልብሱን ይዞ ወስዶ አስባርኮ ይለብሳል ካህኑ ልብሰ ተክህኖውን ሲለብስ ሌሎች ካህናት «ካህናቲከ ይለብሱ ጽድቀ ወጻድቃኒከ ትፍሥሕተ ይትፌሥሑ» ይላሉ ።



ሠ. ካህኑ ልብሰ ተክህኖውን ከለበሰ በኋላ በአንቀጸ ምዕራብ ወደ ቅድስት ወጥቶ ፊቱን ወደ ሕዝቡ አድርጎ «አ እኁየ» የሚለውን ምዕዳንና ጸሎተ ንስሓን ያነብባል ።

ረ. በሥርዓተ ቅዳሴው ላይ የታዘዙትን መዝሙራት ይጸልያል ።

ሰ. ከዚያ ፊቱን ወደ ምሥራቅ መልሶ ከመጋረጃው በአፍአ ሆኖ በሥርዓተ ቅዳሴ የታዘዘውን ይደግማል

«ወአንሰ በብዝኀ ምሕረትከ እበውእ ቤተከ ወእሰግድ ውስተ ጽርሐ መቅደስከ በፈሪሆትከ» እያለ ወደታቦቱ ፊቱን መልሶ አንድ ጊዜ ይሰግዳል ።

ቀ. ከመጋረጃ በአፍአ የሚጸለየውን ጸሎት ከፈጸመ በኋላ አንድ ጊዜ ሰግዶ ወደ መቅደስ ይገባና ጸሎቱን ይቀጥላል፤ በታቦቱ ፊት ሦስት ጊዜ ከሰገደ በኋላ በንዋየ ቅድሳት ላይ የሚጸለየውን ጸሎት ይቀጥላል ።

በ. የማኅፈዱን ጸሎት ይጸልይና ይባርከዋል የጻሕሉን ጸሎት ይጸልይና ይባርከዋል የጽዋውን ጸሎት ይጸልይና ይባርከዋል ፤ የመሶበ ወርቁን ጸሎት ይጸልይና ይባርከዋል ።

ተ. ካህኑ የንዋያተ ቅድሳቱን ጸሎት ከፈጸመ በኋላ ጻሕል ጽዋውን እያለበሰ «እግዚአብሔር ማእምረ ልብ»የሚለውን ጸሎት ይጸልያል፤ከዚያም ንዋያተ ቅድሳቱን ካዘጋጀና በቦታ በቦታቸው ካስቀመጠ በኋላ «አ እግዚእ እግዚአብሔር

www.ethiopianorthodox.org

አምላክነ ዘመሀርከነ ዘንተ ምሥጢረ ዐቢየ» የሚለውን ጸሎት ይጸልያል ።

ኀ. ጸሎቱን ሲጨርስ እጁን ይታጠባል ።

ነ. ዲያቆናቱ መሶበ ወርቁን ይዘው ወደ መቅደስ ሲገቡ «እምነ በሀ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን» ይላሉ ፤ ዕለቱ ረቡዕ ዐርብና ቅዳሜ የሆነ እንደሆነ «መስቀል አብርሀ» ዕለቱ እሑድ ሰንበተ ክርስቲያን የሆነ እንደሆነ «ኵሉ ዘገብራ ለጽድቅ» ይላሉ ።

ካህኑ በመሶበ ወርቁ ላይ እጁን ረብቦ «ተዘከር እግዚኦ እለ አቅረቡ ለከ ዘንተ ቊርባነ» እያለ አንድ ጊዜ መንበሩን ይዞራል ።

አ. ካህኑ በርጥብ እጁ ኅብስቱን ይዞ ይመዘምዛል

ከ. ከመዘመዘው በኋላ ኅብስቱንና ጽዋውን በትእምርተ መስቀል አትሞ ኅብስቱን በሰሜን አንቀጸ መንበር ለንፍቁ ቄስ ይሰጠዋል፤ንፍቁ ቄስ በአንቀጸ ምዕራብ ሆኖ በማኅፈድ ይቀበልና«ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀካህናት በከመ ገነዙከ ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ» የሚለውን ጸሎት እየጸለየ ጠቅልሎ በደቡብ የመንበር በር ይሰጠዋል ።

ካህኑ ኅብስቱን በእጁ ይዞ መብራት የያዘው ንፍቀ ዲያቆን በፊት በፊት ፤ ጽዋ የያዘው ሠራዒው ዲያቆን በኋላው ሆነው እሱ በማህል ሁኖ «እግዚአብሔር አምላክነ ዘተወከፍከ ቊር



ባነ አቤል» እያለ መንበሩን አንድ ጊዜ ይዞራል ። . . .

ወ. ሠራዒ ዲያቆን ወይኑን በጽዋው ይዞ መዝ ፳፪ «እግዚአብሔር ይሬዕየኒ» እያነበበ መንበሩን ይዞራል ።

ዐ. ቀዳስያኑ «ሃሌ ሉያ እመቦ ብእሲ» የሚለውን የሲኖዶሱን ቃል ያውጃሉ ቀጥሎ «አንቲ ውእቱ መሶበ ወርቅ ንጹሕ እንተ ውስቴታ መና ኅቡዕ» እያሉ ይዘምራሉ ፤ በመዋዕለ ጽንጠቀስጤ (በዓለ ሃምሳ)«እመቦ ብእሲ»በሚለው ፋንታ «ሃሌ ሉያ ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ ገነዝዎ ለኢየሱስ» ይባላል ።

ዘ. ከዚህ በኋላ ካህኑ ኅብስቱን በጻሕል ላይ ያኖረዋል ። ይህም ጌታ ወደ መቃብር መውረዱን ለማስታወስ ነው ።
«አንበርነ ዲበ ዝንቱ ጻሕል ቡሩክ በአምሳለ መቃብር ዘነበርከ ውስቴቱ ሠሉሰ ዕለተ ወሠሉስ ለያልየ» እንዲል)
ንፍቅ ካህን ጽዋውን ከዲያቆኑ ተቀብሎ ወይኑን በመንበሩ ላይ በአለው ጽዋ ይቀዳዋል ።

የ. «ቡሩክ እግዚአብሔር» እያለ ኅብስቱን አንድ ጊዜ ወይኑን አንድ ጊዜ ሁለቱንም አንድ ጊዜ አመልካች ጣቱን(ከአውራጣቱ ቀጥሎ ያለውን) አመሳቅሎ ፫ ጊዜ ይባርካል ።
ከዚህ ላይ ፫ የውስጥ ቡራኬ ይጀመራል ካህኑ ቡራኬውን ከአደረገ በኋላ «ተዘከረኒ ኦ አቡየ

www.ethiopianorthodox.org

ቀሲስ»በማለት የእጁን መዳፍ ለሚረዳው ካህን ይሰጣል፤ ተራዳኢውም እጁን በመዳፉ ላይ ጭኖ ይጸልይለታል ።

ደ. ከዚህ በኋላ ካህኑ በሰፊሐ እድ ማለት እጁን ዘርግቶ «አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ»እያለ በዓቢይ ቃል ሃይማኖትን ይመሰክራል ።

ሕዝቡ «በአማን አብ ቅዱስ በአማን ወልድ ቅዱስ በአማን ውእቱ መንፈስ ቅዱስ»ብለው በዜማ ይመልሳሉ ።

ገ. ካህኑና ሕዝቡ «ስብሕዎ ለእግዚአብሔር ኵል ክሙ አሕዛብ» የሚለውን መዝሙር በመ ቀባበልና በመከታተል ይዘምራሉ ።

## ክፍል ሁለት

ሁለተኛው ክፍል ጸሎተ አኰቴት ነው፤

ሀ. ዲያቆን በዜማ «ተንሥኡ ለጸሎት» ይላል፤
ሕዝቡ «እግዚኦ ተሣሃለነ» በማለት ይጸልያሉ
ካህኑ «ሰላም ለኵልክሙ» ይላል፤
ሕዝቡ «ምስለ መንፈስከ» ብለው ይመልሳሉ፤

ለ. ቀጥሎ ካህኑ ጸሎተ አኰቴት «ነአኵቶ ለገባሬ ሠናያት» ብሎ ይጸልያል፤

ሐ. ዲያቆን «ጸልዩ» ይላል ፤

ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልያሉ ፤

መ. ካህኑ ጸሎተ አኰቴትን በመቀጠል «አርኅቅ እግዚኦ እምኔየ» ብሎ ራሱን በመስቀል አንድ



ጊዜ ይባርካል፤«ወእምነ ኵሉ ሕዝብከ»በማለት ፊቱን ወደ ምዕራብ መልሶ ሕዝቡን በመስቀል አንድ ጊዜ ይባርካል «ወእምዝንቱ መካን ቅዱስ» ሲል በመንበሩ ዙሪያ ያሉትን ማለት ልዑካኑን አንድ ጊዜ በመስቀል ይባርካል ፤ በድምሩ ፫ የአፍአ ቡራኬ ይባርካል ፤ የአፍአ ቡራኬ እዚህ ላይ ይጀመራል ።

ሠ. ንፍቅ ዲያቆን«ተንሥኡ ለጸሎት»ይላል ንፍቅ ካህን «ሰላም ለኵልክሙ» ብሎ ጸሎተ መባዕ ይጸልያል ።

ረ. ሠራዒ ዲያቆን «ተንሥኡ ለጸሎት» ይላል በን ባብ ሠራዒ ካህን እንደዚሁ በንባብ «ሰላም ለኵልክሙ» ይልና ጸሎተ እንፎራ (የኅብስትና የወይን መባረኪያ ጸሎት) ይጸልያል፤ በጸሎተ እንፎራ ላይ «አርኢ ገጸከ ላዕለ ዝንቱ ኅብስት» ሲል ወደ ኅብስቱ «ወዲበ ዝንቱ ጽዋዕ»ሲል ወደ ጽዋው ያመለክታል (እማሬ ያደርጋል) እንደዚሁም«ወሚጦ ለዝንቱ ኅብስት» ሲል ወደ ኅብስቱ «ዘተደመረ ውስተ ዝንቱ ጽዋዕ» ሲል ወደ ጽዋው ያመለክታል በድምሩ በዚህ ጸሎት ላይ ፬ እማሬ አለ ።

ሰ. በጸሎተ እንፎራ ላይ «ባርኮ ለዝንቱ ኅብስት» ሲል በኅብስቱ ላይ አንድ ቡራኬ «ወቀድሶ ለዝንቱ ጽዋዕ» ሲል አንድ ቡራኬ በጽዋው ላይ « ወእንጽሖሙ ለክልዔሆሙ» ሲል በሁለቱም ላይ አንድ ቡራኬ በድምሩ ፫ የውስጥ ቡራኬ ይባርካል እስከዚህ ድረስ የውስጥ ቡራኬ ፮ ይሆናል ።

www.ethiopianorthodox.org

ቀ. ካህኑ«አንበርነ ዲበ ዝንቱ ጸሕል» የሚለውን ጸሎተ መግነዝ እየደገመ ኅብስቱንና ጽዋውን ይከድናል ።

በ. ከዚህ በኋላ ዲያቆኑ «ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሀት» ብሎ ሕዝቡን ያዝዛል ።

ሕዝቡ«ቅድሜከ እግዚኦ ንሰግድ» እያሉ ይሰግዳሉ ።

ተ. የሚረዳው ንፍቅ ካህን «ፍትሐት ዘወልድን ይደግማል፤ «ፍትሐት ዘወልድ» ሲደግም ልዑካኑ አድንኖ ያደርጋሉ ፤ በጸሎተ ፍትሐት ዘወልድ ላይ «ወለዙሉ ሕዝብከ ፍትሐሙ» ካለ በኋላ የሐዲሳን ሙታንን ስም ይጠራል «አግብርቲከ እለ ተልእኩ በዛቲ ዕለት ቀሲስ ወዲያቆን ወካህናት » ሲል ሠራዒው ካህን ወደ መንበሩ ካህናቱን አንድ ጊዜ በመስቀል ይባርካል፤ «ወኵሉ ሕዝብ» ሲል ሕዝቡን አንድ ጊዜ በመስቀል ይባርካል፤ «ወምስኪንትየኒ አነ ገብርከ » ሲል ራሱን አንድ ጊዜ በመስቀል ይባርካል በድምሩ በፍትሐት ዘወልድ ጸሎት ላይ ሦስት የአፍአ ቡራኬ አለ ። እስከዚህ ድረስ የአፍአ ቡራኬ ፮ ይሆናል ።

ኀ. ከዚህ በኋላ ንፍቅ ዲያቆን ወደ መቅደስ ይገባና ሙዳየ ዕጣን ለቄሱ ያቀርባል ።
ንፍቅ ካህን ወደ መቅደስ ይገባና ማዕጠንት (ጥና) ለሠራዒው ካህን ያቀርባል፤ ሠራዒው



«ብዘንዜከር» ብሎ መዓልትና ሌሊቱን ከአሠረቀ በኋላ ጸሎተ ዕጣን ይደግማል ።

ነ. ዲያቆን በእንተ ቅድሳትን ይጸልያል ሕዝቡ በየክፍለ ቃሉ» አሜንእግዚኦ ተሣሃለነ»ወይም «አሜን ኪርያላይሶን» ይላሉ ።

አ. ካህኑ አምስት ቆቀር ዕጣን መርጦ ከባረከው በኋላ «አበውዕ ለከ ዕጣነ ምስለ ሐራጊት» እያለ ሦስቱን ቆቀር ዕጣን አንዳንዱን በ፫ቱ ወገን ወደጥናው ያገባል ጳጳስ ከአለ ቄሱ ዕጣኑን በቀኝ እጁ ጥናውን በግራ እጁ ይዞ ለቡራኬ ያቀርብለታል፤ ጳጳስ ባይኖር ግን ቄሱ ራሱ ይባርካል ፤ ካህኑ ዕጣኑን ከጨመረ በኋላ «ስብሐታተ መላእክት» የሚለውን እየጸለየ በምዕራብ በር ቆሞ ምሥዋዑን ያጥናል ።

ከ. «ንስእለከ እግዚኦ ወናስተበቍዓከ ከመ ትዘከራ ለቅድስት አሐቲ ቤተ ክርስቲያን » ከሚለው ጸሎት ሲደርስ እያጠነ ሦስት ጊዜ መንበሩን ይዞራል ቄሱ ዑደት ሲያደርግ መብራት የያዘው ንፍቁ ዲያቆን ከፊቱ ሠራዒው ዲያቆን መጽሐፈ ጳውሎስን በግራ እጁ መስቀል በቀኝ እጁ ይዞ በካህኑ ኋላ ሆኖ ሦስቱም አብረው ይዞራሉ ።

ዲያቆን በመጀመሪያው ዑደት «ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤ/ክርስቲያን» በሁለተኛው ዑደት«ጸልዩ በእንተ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት» በ፫ኛው ዑደት «ጸልዩ በእንተ ማኅበርነ» እያለ ጸሎት ያዝዛል።
ዲያቆኑበዑደትጊዜጸልዩእያለጸሎትሲያዝሕዝቡ

www.ethiopianorthodox.org

«አሜን ኪርያላይሶን እግዚኦ ተሣሃለነ» እያሉ ይጸልያሉ ።

ሊቀ ጳጳሳት ባረፈ ጊዜ በመንበሩ እስኪተካ ድረስ ካህኑ በ፪ኛው ዑደት ላረፈው«ተዘከር እግዚኦ ነፍሰ አቡነ እገሌ»ለሚተካው«ወአን ብር ለነ ዲበ መንበሩ ኖላዌ ኄረ » የሚለውን ይጸልያል ።

ወ. ዑደት ሲያልቅ ዲያቆን በዓቢይ ዜማ«ተንሥኡ ለጸሎት» ይልና ካህኑ ፫ ጊዜ «ንስግድ» እያለ ምሥዋዑን ያጥናል ።

ሕዝቡ «ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ»እያሉ ተሰጦ ይቀበላሉ ።

ዐ. ከዚህ በኋላ ካህኑ«ተዘከሮ እግዚኦለአቡነ እገሌ» እያለ ስለ ጳጳሱ ሦስት ጊዜ ዕጣን ያሳርጋል፤ቀሳ ውስቱን እያንዳንዱን «እስእለከ ኦ አቡየ ቀሲስ ከመ ትዘከረኒ በጸሎትከ ቅድስት»እያለ ዕጣን ያሳርጋል «ቀሳውስቱም እግዚአብሔር ይትወከፍ መሥዋዕተከ ወያጼኑ መዓዛ ዕጣንከ» እያሉ ይመልሱለታል

ዘ. ካህኑ ዲያቆኑን«በረከተ ጳውሎስ ይኅድር በላዕሌከ»በማለት ቦአንብሮት እድ ይባርከዋል ሌሎችን ዲያቆናት«እግዚአብሔር ልዑልይባርከ ወያብርህ አዕይንተ አልባቢከ»እያለ በመስቀል ይባርካል ሕዝቡን ሲባርክ ወንዶችን«እግዚአብሔር ልዑል ይባርከ ወያርኢ ገጾ ላዕሌከ በማለት በመስቀል ይባርካቸዋል፤ ሴቶችን «እግ



ዚአብሔር ልዑል ይባርኪ ወያርኢ ገጾ ላዕሌኪ» በማለት ይባርካቸዋል ።

የ. ከዚህ በኋላ ካህኑ ወደ ቅድስት በምዕራብ በር በቀኝ በኩል ይወርድና« ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ»እያለ በአራቱ መዓዝን በየአንቀጹ እየዞረ ያጥናል ፤ ካህኑ አጥኖ ሲዞር «እግዚአብሔር አምላክነ በከመ አንሀልከ ቅድመ ጥቅማ ለኢያሪኮ» የሚለውን ይጸልያል ዞሮ ሲመለስ በምዕራብ በር በግራ በኩል ወደ መቅደስ ሲገባ «ቦአ መልአክ ኀቤሃ»እያለ እመቤታችንን ያመሰግናል፤ ከገባ በኋላ መንበሩን አንድ ጊዜ እያጠነ ዞሮ ሲመለስ «ኦ ተወካፌ ንስሓ» የሚለውን ጸሎት እየጸለየ በምሥዋዑ ላይ ሦስት ጊዜ ዕጣን ያሳርጋል ።

ደ. ከዚህ በኋላ ንፍቅ ዲያቆን በዓቢይ ዜማ «ተንሥኡ ለጸሎት» ይላል ሕዝቡ «እግዚኦ ተሣሃለነ» ይላሉ ንፍቅ ካህን «ሰላም ለኵልክሙ» ይላል ሕዝቡ «ምስለ መንፈስከ» ይላሉ ቀጥሎ ንፍቁ ቄስ«እግዚኦ አእምሮ ወዜናዌ ጥበብ» የሚለውን ጸሎት ይጸልያል ።

ገ. ሠራዒ ዲያቆን «ኵሎ ዘኢያፈቅሮ» እያለ ወደ ቅድስቱ ከወጣ በኋላ ፊቱን ወደ ምዕራብ አድርጎ የጳውሎስን መልእክት ያነብባል የጳውሎስ ንባብ ሲያልቅ« በረከተ አብ ወፍተ ወልድ ወሀብተ መንፈስ ቅዱስ»ይላል ሕዝቡ «ቅዱስ ሐዋርያ ጳውሎስ» የሚለውን ተሰጦ ይቀበላሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

ጠ. ካህኑ «አ አምላክ ዘለዓለም» የሚለውን ከጸለየ በኋላ ንፍቅ ዲያቆን «ነገር ዘእመልእክተ እገሌ» እያለ ወደ ቅድስቱ ይወጣና ፊቱን ወደ ሰሜን አድርጎ መልእክተ ሐዋርያን ያነብባል የመልእክተ ሐዋርያ ንባብ ሲያልቅ «አ አንውየ ኢታፍቅርዎ ለዓለም» ይላል ። ሕዝቡም «ቅዱስ ሥሉስ ዘኅቡር ህላዌከ» የሚለውን ተሰጥዎ ይቀበላሉ ።

ጀ. ካህኑ «እግዚእነ ወአምላክነ» የሚለውን ጸሎት ይጸልያል «ወዕቀባ ለቤተክርስቲያንከ ቅድስት» ሲል ራሱን አንድ ጊዜ በመስቀል ይባርካል ። «ወባርክ ላዕለ አባግዐ መርዔትከ» ሲል አንድ ጊዜ ሕዝቡን ይባርካል «ወአብዝኅ ለዛቲ ዐጸደ ወይን» ሲል በመንበሩ ዙሪያ ያሉትን አንድ ጊዜ ይባርካል በጠቅላላ ፫ የአፍአ ቡራኬ ያደርጋል ። እስከዚህ የአፍአ ቡራኬ ፱ ይሆናል ።

ጁ. ንፍቅ ካህን «ነቅዕ ንጹሕ ዘእም አንቅዕተ ሕግ ንጹሐን» እያለ ይወጣና ፊቱን ወደ ደቡብ አድርጎ ግብረ ሐዋርያት ያነብባል የግብረ ሐዋርያት ንባብ ሲያልቅ «መልአ ወአብየ ወተለዓለ ቃለ እግዚአብሔር» ይላል ሕዝቡም «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ»የሚለውን ምስጋና በዜማ ይላሉ።

ፀ. ካህኑ «እግዚአብሔር ዘተወክፍከ መሥዋዕተ አቡነ አብርሃም» የሚለውን ጸሎት ከጸለየ በኋላ እንደመጀመሪያውጸሎተ ዕጣን «ንስእለከ ወናስተበ ቍዓከ» የሚለውን እየጸለየና እያጠነ ሦስት ጊዜ መንበሩን ይዞራል ፤አሁንም ንፍቁ ዲያቆን መስብራት ይዞ በፊቱ ፤ ሠራዒው ዲያቆን መስቀልይዞ በኋላው ሆኖ አብረው ተከታትለው ይዞራሉ ከዑደት በኋላ ካህኑ «ተፈሥሒ አ ዘንስእለኪ ዳኅና»እያለወደ እመቤታችን ይማፀናል ።



ፈ. ከዚህ በኋላ በስተምዕራብ ከመንጦላዕቱ በውጭ ቀዳሾች ዲያቆናች ፊታቸውን ወደ ምዕራብ ቀሳውስቱ ፊታቸውን ወደ መንበሩ መልሰው በመቀባበል «ዝውእቱ ጊዜ ባርኮትን » በዜማ ይላሉ ሲቀባበሉም ቀሳውስቱ «ዝውእቱ» ሲሉ ዲያቆናቱና ሕዝቡ «ዕጣን ይእቲ ማርያም» እያሉ ነው ።

ፐ. በመዋዕለ ጽንጠቆስጤ (በዓለ ሃምሳ) በዝውእቱ ፋንታ «ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን» ይባላል ።

## ክፍል ሦስት

፫ኛው ክፍል ኪዳን ነው ፤

ሀ. ካህኑ «ቅዱስ» ይልና ኪዳን ይደርሳል ፤

ለ. ቅዳሴው ሌሊት ከሆነ ወይም ነግህና ሠለስት የሆነ እንደሆነ ኪዳን ፪ኛ ክፍል «እግዚአብሔር አብ ወሃቤ ብርሃን» ይባላል ሠርክ የሆነ እንደሆነ የሠርክ ኪዳን «ለከ ለአብ ዘኢይማስን» ይባላል ።

ሐ. ከኪዳን ቀጥሎ ሕዝቡ «አ ሥሉስ ቅዱስ መሐረነ» የሚለውን በዜማ ይላሉ

መ. ካህኑ «ሃሌ ሉያ ለአብ ተፈሥሒ ተፈሥሒ» ሲል ሕዝቡ «እግዚአብሔር ምስሌኪ»እያሉ በመቀባበል ይዘልቃሉ ቀጥሎ «ካህኑ ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ»ይላል።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል አራት

፬ኛው ክፍል ጸሎተ ወንጌል ነው ፤

ሀ. ዲያቆን በዓቢይ «ተንሥኡ ለጸሎት» ይላል ካህኑ «እግዚአብሔር እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ» የሚለውን ጸሎተ ወንጌል ያደርሳል ። ዲያቆን «ጸልዩ በእንተ ወንጌል ቅዱስ» ሕዝቡም «ረስየነ ድልዋነ ለሰሚዐ ወንጌል ቅዱስ» ይላሉ ፤ ካህኑ «ተዘከር ካዕበ »ብሎ ይጨርሳል ፤

ለ. ዲያቆኑ ከመዝሙረ ዳዊት ምስባክ በዜማ ይሰብካል ሕዝቡ ምስባኩን ይቀበላሉ ዲያቆኑ ምስባኩን መልሶ ይሰብካል ሕዝቡም ደግመው ይቀበላሉ በሦስተኛው ምስባኩን ሕዝቡ ብቻ ይላሉ ፤

ሐ. ከዚህ በኋላ ካህኑ «እግዚአብሔር ልዑል ይባርክ ላዕለ ኵልነ» እያለ አራቱን ማዕዘን በመስቀል ይባርካል ፤ ወዲያው «እግዚአብሔር አምላክነ·······አንተ ውእቱ ዘፈነውኮሙ ለአርዳኢከ» የሚለውን ይጸልያል ።

መ. ከዚህ በኋላ ካህኑ አንድ ቀቀር ዕጣን በማዕጠንቱ ጨምሮ መብራት የያዘ ንፍቅ ዲያቆን በፊቱ ፣ ንፍቅ ካህን ወንጌሉን ይዞ፣ ንፍቁን ዲያቆን በመከተል ሠራዒው ካህን ማዕጠንት ይዞ በመካከል ሆኖ እያጠነ ፥ ሠራዒ ዲያቆን መስቀል ይዞ



ሠራዒውን ካህን ተከትሎ ይዞራሉ ። መንበሩን ዞረው በአንቀጸ ምዕራብ ሲደርሱ ንፍቅ ካህን በምሥዋዑ ፊት ለፊት ሆኖ ወደ ምዕራብ ፊቱን መልሶ ወንጌሉን ገልጦ ይቆማል ፤ ካህኑ «ቡሩክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ዓለም አምላክነ ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ» እያለ በማዕጠንት ወንጌሉን ያጥናል ካህኑ «ቡሩክ» እያለ ወደ ወንጌሉ በሚያጥንበት ጊዜ ንፍቁ ካህን «አዕኵትዎ ለአብ አዕኵትዎ ለወልድ አዕኵትዎ ለመንፈስ ቅዱስ» እያለ ይመልሳል ወንጌሉን ለካህኑ ሰጥቶ ማዕጠንቱን ይቀበላል ።

ሠ. ካህኑ ወንጌሉን ከንፍቁ ካህን ሲቀበል አይቶ ዲያቆኑ በምዕራብ በር ሆኖ ፊቱን ወደ ምሥራቅ አድርጎ «ሃሌ ሉያ» ካለ በኋላ እንደገና ፊቱን ወደ ምዕራብ መልሶ «ቁሙ ወአጽምዑ ወንጌለ ቅዱሰ» ብሎ ሕዝቡን ያዝዛል ።

ረ. ካህኑ ለሕዝቡ ወንጌሉን እያሳየ ፊቱን ወደ ሕዝቡ መልሶ «እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ» ካለ በኋላ ወንጌሉን ዘርግቶ በታላቅ ዜማ «ወንጌል ቅዱስ» ይልና መንበሩን ዞር በምዕራብ በር በቀኝ በኩል ወደ ቅድስት ይወርዳል ፤ በዚህ ጊዜ መብራት የያዘ ንፍቅ ዲያቆን በፊት ማዕጠንት የያዘ ንፍቅ ቄስ፣ወንጌሉን የያዘ ካህን

www.ethiopianorthodox.org

በመከታተል ሠራዒ ዲያቆን በኋላ ሆነው ተከ ታትለው ይወጣሉ ።

ሰ. ካህኑ «ነዋ ወንጌለ መንግሥተ ሰማያት» ይልና ወንጌሉን ለንፍቁ ካህን ይሰጠዋል ።

ንፍቁ ካህን «መንግሥቶ ወጽድቆ ዘአወፈየኒ አወፈይኩከ» ይልና ወንጌሉን ተቀብሎ ለዲ ያቆኑ ይሰጠዋል ፤ ዲያቆኑ « ነሥሑ እስመ ቀር በት መንግሥተ ሰማያት» በማለት ወንጌሉን ይቀበልና ይይዛል። ካህኑ መስቀሉን ከዲያቆኑ ይቀበልና በቀኝ እጁ ይዞ ፊቱን ወደ ምሥራቅ መልሶ ወንጌሉን ያነብባል ።

ሸ. ካህኑ ወንጌሉን ሊያነብ ሲል የወንጌላዊውን ስም እየጠራ «ባርክ እግዚኦ ነገረ ዘእምወንጌለ እገሌ» ይላል በዮሐንስ ወንጌል ግን« ዝ ቃል ዘእ ግዚእነ ወአምላክነ» ይላል ፤ ወንጌል ከተነበበ በኋላ በመጨረሻ ካህኑ በማቴዎስ «ሰማይ ወምድር የኀልፍ ወቃልየሰ ኢየኀልፍ ይቤ እግ ዚእ ለአርዳኢሁ» በማርቆስ «እንዘ እግዚእ ይረ ድዕ ወቃሎ ያጸንዕ በትእምርት ዘይተሉ ዘበ ዕዝነ ሰሚዐ ለይስማዕ ይቤ እግዚእ ለአርዳኢሁ» በሉቃስ «ይቀልል ኀልፈተ ሰማይ ወምድር እም ትደቅ አሐቲ ቃል እምኦሪት ወእምነቢያት ይቤ እግዚእ ለአርዳኢሁ » በዮሐንስ«ዘየአምን በወልድ ቦ ሕይወት ዘለዓለም» ብሎ ሲፈጽም ሕዝቡ የወንጌሉን መርገፍ በኅብረት ይላሉ ።

ቀ. ወንጌል ከመነበቡ በፊት ንፍቅ ካህን «ርኁቀ መዓትን» ይጸልያል ።



በ. ሠራዒው ካህን ወንጌሉን አንብቦ ሲጨርስ ንፍቁ ቄስ «ስብሐት ለከ እግዚአብሔር . . .» የሚለውን ጸሎት ይጸልያል ።

ተ. ካህኑ አንብቦ ከፈጸመ በኋላ ወንጌሉን ያሳ ልማል ፤ ሕዝቡ ወንጌሉን ሲሳለሙ «ነአምን በቃለ ወንጌል ቅዱስ » እያሉ በቃለ ወንጌል ማመናቸውን ይመሰክራሉ ።

ቸ. ጸሎተ ወንጌል ከተፈጸመ በኋላ ንፍቅ ዲያቆን መብራት ይዞ በፊት ንፍቅ ካህን ማዕጠንት ይዞ በኋላ ሆኖ ሁለቱም በቅድስት በቀኝ በኩል ዞረው በሰሜን የመቅደሱ በር ይገባሉ ።

ኀ. ዲያቆን በቅድስቱ ላይ ሆኖ ፊቱን ወደ ምዕራብ መልሶ ቃጭል እየመታ «ፃኡ ንኡሰ ክር ስቲያን» ይላል ይህንንም የሚያውጅበት ምክንያት ንኡሰ ክርስቲያን የሚባሉት የክ ርስትና ሃይማኖትን በማጥናትና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በመከታተል ላይ ያሉት ገና ያል ተጠመቁት ሰዎች ስለሆኑ ለመቍረብ ስለማ ይችሉ ነው ።

## ክፍል ፫

፫ኛው ክፍል ጸዋትው ነው ። ጸዋትው ማለት ስለ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን ስለ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ስለ ማኅበረ ምእመናን የሚጸለየው ጸሎት ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ሀ. ካህኑ ወደ መቅደስ ገብቶ በታቦቱ ፊት «እግዚአብሔር አምላክነ ዘበእንተ አፍቅሮትከ ሰብአ ፈነውኮ ለወልድከ ዋሕድ »የሚለውን ጸሎት ይጸልያል ።

ለ. ከዚያ በኋላ ካህኑ ስለ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን ይጸልያል፤ «ኵሎ ሕዝበ ወኵሎ መራዕየ ባርኮሙ» ሲል አንድ ጊዜ ሕዝቡን በመስቀል ይባርካል እስከዚህ ድረስ የአፍአ ቡራኬ አሥር ይሆናል ።

ሐ. ዲያቆን «ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን» ይላል ሕዝቡ «ኪርያላይሶን (እግዚኦ ተማሃለነ» ይላሉ ።

መ. ንፍቅ ዲያቆን «ተንሥኡ» ይልና ንፍቅ ካህን ስለ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ይጸልያል ፤ ንፍቁ ዲያቆን «ጸልዩ በእንተ ሊቅነ» በማለት ስለጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ስለ ቀሳውስትና ዲያቆናት ስለ ሕዝበ ክርስቲያንም ሁሉ እንዲጸልዩ ሕዝቡን ያዝዛል ሕዝቡም አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልያሉ።

ሠ. ዲያቆን «ተንሥኡ» ይልና ካህኑ ስለማኅበረ ምእመናን ይጸልያል ፤ «ተዘከር እግዚኦ ማኅበረነ ባርኮሙ» ሲል ሕዝቡን አንድ ጊዜ በመስቀል ይባርካል ፤ እስከዚህ ድረስ የአፍአ ቡራኬ ፲፩ ይሆናል ።

ረ. ዲያቆን «ጸልዩ በእንተ ዛቲ ቤተ ክርስቲያን» ብሎ ጸሎት ያዝዛል ፤ ሕዝቡ «ማኅበረነ ባርክ ዕቀብ በሰላም» በማለት ይጸልያሉ ።



ሰ. ዲያቆን «ወንበል ኵልነ በጥበበ እግዚአብሐር ጸሎተ ሃይማኖት»ወይም «በጥበበ እግዚአብሐር አውሥኡ ጸሎተ ሃይማኖት» ብሎ ያዝዛል ፤ ሕዝቡም ቅዳሴው የሊቃውንት ከሆነ ጸሎተ ሃይማኖትን ይጸልያሉ ፤ ፍሬ ቅዳሴው ቅዳሴ እግዚእ ቅዳሴ ሐዋርያት ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ የሆነ እንደሆነ አመክንዮ ዘሐዋርያትን ይጸልያሉ ።

ቀ. ካህኑ «ተዘከር እግዚኦ ማኅበረነ» የሚለውን ጸሎት ከፈጸመ በኋላ ማዕጠንቱን አንሥቶ በምሥዋዑ ላይ ፫ ጊዜ ዕጣን ያሳርጋል ፤ ምሥዋዑን ከአጠነ በኋላ በአድንኖ ርእስ በመንበሩ ፊት አራቱን ማዕዘን አጥኖ ለንፍቁ ካህን ማዕጠንቱን ይሰጣል ።

ክፍል ፮

ስድስተኛው ክፍል ፍሬ ቅዳሴ ነው ።

ሀ. ጸሎተ ሃይማኖት ከተባለ በኋላ ካህኑ «ዘኮነ ንጹሐ ይንሣእ እምቍርባን» እያለ ያውጃል ፤ በዚህ ጊዜ እጁን በሕዝቡ ፊት ይታጠብና ማዩን በእጁ እንደያዘ «በከመ አንጽሕኩ እደውየ------» በማለት ሐላፊነትን አስረድቶ በሕዝቡ ፊት ይረጨዋል ።

ለ. ዲያቆን በምዕራብ በር ብቅ ብሎ ፊቱን ወደ ሕዝቡ አድርጎ «እመቦ ዘአስተሐቀረ ዘንተ ቃለ ቀሲስ» የሚለውን ዐዋጅ ያውጃል፤ቀጥሎ ካህኑ

www.ethiopianorthodox.org

«እግዚእየ ወአምላኪየ ገባሬ ሥርዓት ወሀቤ ሰላም ወፍቅር አሰስል እምላዕሌየ ኵሎ ሕሊና እኩየ» የሚለውን ይጸልያል በዚህ ጊዜ ንፍቅ ካህን ኀብስቱ የተሸፈነበትን ማኀፈድ ይገልጣል ።

ሐ. ከዚህ በኋላ ዲያቆን በዓቢይ ዜማ «ተንሥኡ ለጸሎት» ይላል ሕዝቡ «እግዚኦ ተሣሃለነ» ካህኑ «ሰላም ለኵልክሙ» ሕዝቡ «ምስለ መንፈስከ» ይላሉ ።

ከዚህ በኋላ ካህኑ «እግዚአብሔር ዓቢይ ዘለዓለም» የሚለውን ይጸልያል ፤ በዚሁ መካከል ካህኑ «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት» ሲል ሕዝቡ ተቀብለው «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት» እያሉ ያመሰግናሉ ። ቀጥሎ ካህኑ «አ እግዚኦ በሥምረትከ ምላእ ውስተ አልባቢነ ----» የሚለውን ሲጸልይ ዲያቆኑ «ጸልዩ በእንተ ሰላም - - - - ተእምኑ በበይናቲክሙ» ብሎ ሕዝቡን ያዝዛል ሕዝቡም «ክርስቶስ አምላክነ ረስየነ ድልዋነከመ ንትአማኅ በበይናቲነ» በማለት ይጸልያሉ ይህንንም እየጸለዩ ርስበርሳቸው እማኄ ያደርጋሉ ።

መ. ካህኑ ከእማኄው ቀጥሎ «ወንትመጦ እንበለ ሙነኔ እምሀብትከ ቅድስት --- » ብሎ ከፈጸመ በኋላ የዕለቱን ፍሬ ቅዳሴ ይጀምራል ።

ሠ. ከጸሎተ ቡራኬ ሲደርስ ዲያቆን «በእንተ ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አባ እገሌ» ብሎ የቅዱስ ፓትርያርኩን ስም ከጠራ በኋላ



« ወብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አባ እገሌ» ብሎ የሀገረ ስብከቱን ሊቀ ጳጳሳት ስም ይጠራል ።

ረ. ንፍቅ ካህን ጸሎተ ቡራኬ ይጸልያል ፤ በጸሎቱ ላይ «ባርክ» የሚል ቃል ሲያነግ ሠራዒ ካህን በእጁ ይባርካል ፤ በዚህ ጸሎት ላይ ፫ የአፍአ ቡራኬ አለ እስከዚህ ድረስ የአፍአ ቡራኬ ፲፬ ይሆናል ።

ሰ. ጸሎተ ቡራኬ ሲያልቅ ንፍቅ ዲያቆን «መሐሮሙ እግዚኦ»በማለ ት ስለ ሊቃነ ጳጳሳት ስለ ኤጲስ ቆጶሳት ስለ ቀሳውስትና ዲያቆናት ስለ ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ ይጸልያል ።

ቀ. ዲያቆን ቅዳሴው በሚያዝዘው በየሥፍራው «እለ ትነብሩ ተንሥኡ፤ውስተ ጽባሕ ነጽሩ፤ ንነጽር፤ አውሥኡ»እያለ ለሕዝቡ ያዘክራል ። «አውሥኡ» ሲል ሕዝቡ ተሰጥዎውን«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር» እያሉ ያመሰግናሉ ቀጥሎ ከቦታው ሲደርስ ሕዝቡ «ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ»እያሉ ይጸልያሉ ። ሕዝቡ«ተዘከረነ»ሲሉ ንፍቅ ካህን አንድ ቆቀር ዕጣን ወግሮ ለካህኑ ማዕጠንቱን ያቀርብለታል ። ካህኑ ጢሰ ዕጣኑን በሁለት እጁ እየታፈነ ሦስት ጊዜ ከኅብስቱ ሦስት ጊዜ ከወይኑ ያሳርጋል ።

ተ. ዲያቆን «አንሥኡ እደዊክሙ ቀሳውስት» በማለት ካህኑ ኅብስቱን ፣ ንፍቁ ካህን ማኀፈዱን ከጻሕሉ ላይ እንዲያነሡ ያሳስባል ፤ በዚህ ጊዜ ካህኑ

www.ethiopianorthodox.org

ኅብስቱን ሲያነሣ ንፍቁ ካህን ማኅፈዱን ይገልጥለታል ንፍቁ ማኅፈዱን ከአነሣለት በኋላ ካህኑ ኅብስቱን በጻሕሉ ላይ ያኖረዋል ።

ኀ. ካህኑ በጸሎተ ቅዳሴው ውስጥ «አዕኰተ ባረከ» ሲል ጣቱን አመሳቅሎ ሦስት ጊዜ በእጁ ኅብስቱን ይባርካል ፤ «ወፈተተ» ሲል አምስት ላይ ኅብስቱን በጣቱ ይወገዋል እዚህ ላይ ፩ የውስጥ ቡራኬ አለ እንደዚሁም በጽዋው ላይ «አዕኰተ ባረከ» ሲል እንደላይኛው ወይኑን ሦስት ጊዜ በእጁ ይባርክና በትእምርተ መስቀል በጣቱ የጽዋውን ከንፈር እየያዘ ይወዘውዘዋል ከእዚህም ላይ ሦስት የውስጥ ቡራኬ አለ በአጠቃላይ እስከዚህ ድረስ ፲፪ የውስጥ ቡራኬ ይሆናል ። ካህኑ ሥጋውንና ደሙን ሲባርክ ሕዝቡ«አሜን ነአምን»እያሉ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወይኑ ተለውጦ ደመ ወልደ እግዚአብሔር መሆኑን በማመን ይመሰክራሉ ።

ነ. «ዝ ውእቱ ሥጋየ» ሲል ወደ ሥጋው ያመለክታል «ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ»ሲል ወደ ደሙ ያመለክታል ከዚህ ላይ ሁለት እማሬ አለ በድምሩ እስከዚህ ድረስ ፬ እማሬ ይሆናል ።

አ. ይረስዮ «ለዝንቱ ኅብስት»ሲል አንድ ጊዜ ኅብስቱን «ወለዝንቱ ጽዋዕ» ሲል አንድ ጊዜ ጽዋውን እንደ ገና ሁለቱንም በአንድነት አንድ ጊዜ ይባርካል በድምሩ ፫ ቡራኬ ያደርጋል ፤



እስከዚህ ድረስ ፲፭ የውስጥ ቡራኬ ይደረጋል እዚህ ላይ በኅብስቱ አንድ አማሬ በጽዋው አንድ አማሬ ያደርጋል ፤ በድምሩ ሁለት አማሬ አለ እስከዚህ ድረስ ፮ አማሬ ይሆናል ።

ከ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ «አሜን እግዚኦ መሐረነ» እያሉ ይጸልያሉ ።

ወ. ዲያቆን «በኵሉ ልብ ናስተብቍዖ ለእግዚአብሔር አምላክነ ---» ይላል ሕዝቡ «በከመ ሀሎ ሀልወ » ይላል ፤

ዐ. ካህኑ «ደሚረከ ተሀበሙ» እያለ ሥጋውን በደሙ ያትማል ።

## ክፍል ሰባት

ሰባተኛው ክፍል ጸሎተ ፈትቶ ነው ፤

ሀ. ካህኑ ጸሎተ ፈትቶውን እየጸለየ ኅብስቱን አሥራ ሦስት ቦታ ይፈትተዋል ፤ ሲፈትትም ከላይ ወደ ታች እየፈተተ ይወርዳል፤መሀል መሀሉን ከቀኝ ወደ ግራ ከግራ ወደ ቀኝ እያለ ይፈትተዋል ፤ ዙሪያውን ይፈትተዋል፤በመጨረሻ ከታች ወደ ላይ እየፈተተ ይወጣል ከፈተተ በኋላ ዘባኑን ሳይለይ ከሦስት ይከፍለዋል ።
በሁለተኛው ጸሎተ ፈትቶ የላዩን ወደታች የታቹን ወደላይ የቀኙን ወደ ግራ የግራውን ወደቀኝ ያስተላልፍበታል ።
በሦስተኛው ጸሎተ ፈትቶ በቦታ በቦታው ይመልሰዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ለ. ካህኑ የመጀመሪያውን ጸሎተ ፈትቶ ሲጨርስ ዲያቆን «ጸልዩ» ይላል ሕዝቡ «አቡነ ዘበሰማያት» በዜማ ይጸልያሉ ።

ሐ. ካህኑ ሁለተኛውን ጸሎተ ፈትቶ ጸልዩ ሲጨርስ ሕዝቡ «በከመ ምሕረትከ አምላክነ» ይላሉ ከዚህ በኋላ ንፍቅ ካህንና ንፍቅ ዲያቆን ከመጋረጃ ውጭ ሁነው ሌሎች ከመጋረጃ ውስጥ ሆነው «ሠራዊተ መላእክቲሁ ----» የሚለውን እየተቀባበሉ ሦስት ጊዜ በዜማ ይላሉ ።

መ. ቀጥሎ ንፍቅ ዲያቆን ከመጋረጃ ውጭ ሁኖ ፊቱን ወደ መንበሩ አድርጎ « አርኅዉ ኆኃተ መኳንንት» በማለት የመቅደሱ በር እንዲከፈት ያሳስባል ፤ በዚህ ጊዜ ዲያቆን በሩን ይከፍታል ።

ሠ. ዲያቆን ሠራዒ « እለ ትቀውሙ አትሕቱ ርእሰክሙ» ብሎ አድንኖ እንዲያደርጉ ያዝዛል ።

ረ. በዚህ ጊዜ ካህኑ በሐዋርያት ቅዳሴ «እግዚአብሔር ዘለዓለም ማእምር ዘኅቡዕ ወዘገሐድ» የሚለውን በሌሎችም ቅዳሴያት በዚህ ቦታ የታዘዘውን ይጸልያል ቀጥሎ ዲያቆኑ «ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሀት» ይላል ሕዝቡም «ቅድሜከ እግዚኦ ንሰግድ ወንሴብሐከ»በማለትይሰግዳሉ።

ሰ. ካህኑ ጸሎተ ንስሐ ይጸልያል ፤ በጸሎተ ንስሐ «ኦ እግዚኦ ረስየነ ፍቱሐነ ወግዑዛነ ወለኵሎሙ ሕዝብከ ፍትሐሙ» ሲል ሕዝቡን ፫ ጊዜ



ይባርካል፤እዚህ ላይ ሦስት የአፍአ ቡራኬ ሲደረግ በጠቅላላው እስከዚህ ድረስ ፲፰ የአፍአ ቡራኬ ይሆናል ፤ በዚህም ላይ በቅርብ ጊዜ የሞቱትን ሰዎች ስም ይጠራል ፤ ጸሎተ ንስሐ ሲፈጽም ዲያቆን «ነጽር» ይላል ካህኑ«ቅድሳት ለቅዱሳን» ይላል ሕዝቡ «አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ » ይላሉ ።

ቀ. ካህኑ ፊቱን ወደ ምዕራብ መልሶ «እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ»ይላል ፤ ሕዝቡ«ምስለ መንፈስከ» ይላሉ ።

በ. ካህኑ ኅብስቱን ከጻሕሉ ላይ አንሥቶ በሁለት እጁ ወደላይ ይዞ በዓቢይና በንኡስ ዜማ«እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ» ይላል ፤ ሕዝቡም ካህኑን ተከትለው«እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ» ይላሉ ካህኑና ሕዝቡ እግዚኦታውን ፵፩ ጊዜ ይላሉ በመቀባበል ። ፵፩ኛውን እግዚኦታ ካህኑ ብቻውን ይለዋል ።

ተ. እግዚኦታው ሲያልቅ ዲያቆኑ«እለ ውስተ ንስሐ ሀሎክሙ አትሕቱ ርእሰክሙ»ይላል ፤ ሕዝቡም ራሳቸውን ዘንበል ያደርጋሉ ፤ ካህኑ «እግዚአብሔር አምላክነ ነጽር ዲበ ሕዝብከ እለ ውስተ ንስሐ ሀለዉ» የሚለውን ጸሎት ይጸልያል ።

ኀ. ጸሎቱ ሲያልቅ ዲያቆኑ በንባብ «ተንሥኡ ለጸሎት»ይላል ሕዝቡም «እግዚኦ ተሣሃለነ» ይላሉ ካህኑ«ሰላም ለኵልክሙ»ይላል፤ሕዝቡም«ምስለ

www.ethiopianorthodox.org

መንፈስከ» ይላሉ ካህኑ «ሥጋ ቅዱስዘበአማን» ይላል ፤ ሥጋ ቅዱስ ዘበአማን ሲል ሕዝቡ በየ ምዕራፉ«አሜን»ይላሉ፤«ሥጋ ቅዱስ ዘበአማን ዝ ውእቱ ዘእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ» ሲል ወደ ኅብስቱ እማሬ ያደርጋል «ደም ክቡር ዘበአማን ዝ ውእቱ ዘእግዚእነ- - -» ሲል ወደ ጽዋው እማሬ ያደርጋል ፤«እስመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ ለአማኑኤል አምላክነ» ሲል ወደ ኅብስቱና ወደ ጽዋው በአንድነት አንድ እማሬ ያደርጋል ፤ እስከዚህ ድረስ በጠቅላላው እማሬ ፲፩ ይሆናል ፤እማሬ በዚህ ይፈጸማል ።

«አአምን አአምን አአምን ወእትአመን» በሚልበት ጊዜ ዕስበ ዲያቆኑን በደሙ ጠምቶ በመጀመሪያው ያለውን ዐቢዩን ክፍል ይባርካል ። በ፪ኛው «አአምን» በመካከል ያለውን ክፍል ይባርካል ፤ በ፫ኛው «አአምን» ንኡሱን ክፍል ይባርካል ፤ እዚህ ላይ ፫ የውስጥ ቡራኬ አለ እስከዚህ ድረስ የውስጥ ቡራኬ ፲፰ ይሆናል ።

ነ. ሥጋውን በደሙ ካተመ በኋላ «ቡሩክ እግዚአብሔር» እያለ ደሙን በሥጋው ሦስት ጊዜ ይባርካል፤እዚህም ላይ የውስጥ ቡራኬ ፫ ነው በጠቅላላው እስከዚህ ድረስ የውስጥ ቡራኬ ፳፩ ይሆናል የውስጥ ቡራኬ እዚህ ላይ ይፈጸማል ።

አ. ካህኑ ደሙን በሥጋው ከባረከ በኋላ ዕስበ ዲያቆኑን በጽዋው ውስጥ ይጨምረዋል ።



ከ. የሥጋው የደሙ ቡራኬ ከአበቃ በኋላ ልዑካኑ እጃቸውን ይታጠባሉ ።

ወ. ካህኑ «አ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ኢይኩን ዝንቱ ምሥጢርከ አበሳ ላዕሌየ - - -»የሚለውን ጸሎት ጸልዮ ሥጋውን ራሱ አንሥቶ ይቀበላል ደሙን ንፍቁ ቄስ ያቀብለዋል ። ለካህናቱ ለዲያቆናቱና ለንፍቀ ዲያቆናቱ በየማዕርጋቸውርሱ ያቀብላል ፤ ከመቅደስ ወጥቶም ለሕዝቡ በየማዕርጋቸው ያቀብላል ቄሱ ሥጋውን ሲያቀብል የተቀደሰው ቅዳሴ ሐዋርያት ከሆነ «ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት» እያለ ያቀብላል ፤ የተቀደሰው ቅዳሴ እግዚእ ከሆነ «ሥጋሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ» እያለ ያቀብላል ፤ የተቀደሰው ቅዳሴ ሊቃውንት ከሆነ «ሥጋሁ ለአማኑኤል አምላክነ» እያለ ያቀብላል ፤ ሠራዒው ካህን ሥጋውን ሲያቀብል ንፍቅ ካህን ደሙን በዕርፈ መስቀሉ ያቀብላል በመጀመሪያ ለዲያቆኑ ዕስበ ዲያቆኑን (ወደ ጽዋው የገባውን መካከለኛውን መስቀል) በዕርፈ መስቀሉ ይሰጠዋል ፤ ንፍቁ ካህን ደሙን ሲያቀብል «ዝንቱ ጽዋዐ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት» እያለ ያቀብላል፤ ካህኑ ለሕዝቡ ሥጋውን ሲያቀብል ዲያቆን ጽዋውን ከንፍቁ ካህን ተቀብሎ በዕርፈ መስቀል ደሙን ያቀብላል ።

ዐ. ሕዝቡ ሥጋውን ደሙን በሚቀበሉበት ጊዜ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሥሉስ ዘኢይትነገር» የሚ

www.ethiopianorthodox.org

ለውን ይጸልያሉ፤ ሲቈርቡ ሥጋውን ሲቀበሉ አንድ ጊዜ«አሜን»ደሙን ሲቀበሉ «አሜን ወአሜን»ይላሉ ።

ዘ. «ክብር ይእቲ ዛቲ ለኵሉ ጻድቃኑ» ብሎ ካህኑ እየመራ ሁሉም አንድ ሆነው«ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር በቅዱሳኑ» የሚለውን መዝሙረ ዳዊት ይዘምራሉ ።

ደ. ድርገት ሲወርዱ ካህኑ «አለ ጸዋዕከ»በማለት በጸሕል ላይ አንድ የእፍኦ ቡራኬ ይባርካል ።

ገ. ሕዝቡ ከቈረቡ በኋላ ዲያቆን ጽዋውን እንደ ያዘ በቅድስት እየዞረ «ንእኵቶ ለእግዚአብሔር ቅድሳቶ ንሢኦ» ይላል ።

ጠ. ዲያቆን«ንእኵቶ»ሲል ካህኑ በዓለ እግዚአብሔር በዓለ ማርያም እሑድ ሰንበት የሆነ እንደሆነ አሌለክን ይላል ፤ ዕለቱ ዘወትር የሆነ እንደሆነ «ስብሐተ እግዚአብሔር ይነግር አፉየ»ይላል ፤ ሕዝቡ «አቡነ ዘበሰማያት ኢታብአነ እግዚአ ውስተ መንሱት» ይላሉ ።

## ክፍል ስምንት

ስምንተኛው ክፍል የሐዳፌ ነፍስ ጸሎት ነው ፤

ሀ. ካህኑ የሐዳፌ ነፍሱን ጸሎት ይጸልያል፤ሐዳፌ ነፍሱ«ጸልዩ» ያለበት ከሆነ «ጸልዩ»እስከሚል ድረስ ፊቱን ወደ ምዕራብ ይመልሳል ፤ ጸልዩ ከአለ በኋላ ፊቱን ወደ ምሥራቅ ይመልሳል፤ «ጸልዩ»የሌለው ከሆነ በሙሉ ፊቱን ወደ ምሥ



ራቅ እንደ መለሰ ይጨርሳል፤«ጸልዩ» ያለበት የሐዳፌ ነፍስ ጸሎት ጸልዩ እስከሚል ያለውን ካህኑ ወደ ምዕራብ ዞሮ ማለቱ ጌታ በዕለተ ዓርብ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ነፍሳትን ማውጣቱን ለማዘከር ነው ፤ ፩. ጴጥሮስ ፫.፲፱ ጸልዩ ካለ በኋላ ያለውን ወደ ምሥራቅ ዞሮ ማለቱ ጌታ ነፍሳትን ከሲኦል አውጥቶ ወደ ገነት ማግባቱን ለማዘከር ነው ።

ለ. ካህኑ የሐዳፌ ነፍሱን ጸሎት ሲጨርስ ምሥጢር አኰቴት የሚባለውን ዝማሬ ይዘምራል ዝማሬውን ሲጨርስ ሁሉም«ሃሌ ሃሌ ሉያ አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ - - -»የሚለውን ዕጣነ ሞገር ይዘምራሉ ።

ሐ. ከዚህ በኋላ ያለውን ካህኑ መጽሐፈ ቅዳሴው እንደሚያዝዘው ፈጽሞ«መልአተ እግዚአ ምሥጢርከ»የሚለውን ጸሎት ይጸልያል ከዚህ በኋላ ልኡካኑ ሁሉም አንድ ሆነው እየአንዳንዱ «እጼሊ ኀቤከ- - -»የሚለውን ጸሎት ይጸልያሉ።

መ. ዲያቆን «በእንተ አኰቴትነ ናስተበቍዕ - - » የሚለውን ጸሎት ይጸልያል ።

## ክፍል ዘጠኝ

ዘጠነኛው ክፍል አንብሮ እድና ሠርሆተ ሕዝብ ነው ።

ሀ. ካህኑ እጁን በታቦቱ ላይ አድርጎ«አንብሮ እድ» ይጸልያል ።

www.ethiopianorthodox.org

ለ. ንፍቅ ካህን «ወዕቀቦሙ» የሚለውን ጸሎት በድርገት መውረጃው ላይ ሆኖ ለሕዝቡ ይጸልያል ፤ ሕዝቡም «አንገሥ ሰላም ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላመከ ሀበነ - - -» የሚለውን ጸሎት ይጸልያሉ ፤

ሐ. ዲያቆን «አድንኑ አርእስቲክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ በእደ ገብሩ ካህን ከመ ይባርክነ» ይላል ፤ ሕዝቡ «አሜን እግዚአብሔር ይባርከነ ወይሠሃለነ» ብለው ራሳቸውን ዘንበል ዘንበል ያደርጋሉ ።

መ. ሠራዒው ካህን «ኦ እግዚኦ አድኅን ሕዝበከ ወባርክ ርስተከ» እያለ ሕዝቡን ሦስት ጊዜ በመስቀል ከባረከ በኋላ «ረዐዮሙ ወአልዕሎሙ እስከ ለዓለም»የሚለውን ጸሎት ቡራኬና ጸሎተ አስተስርዮ ይጸልያል ፤ እስከዚህ ድረስ የአፍአ ቡራኬ በጠቅላላው ፳፩ ይሆናል ።

ሠ. ካህኑ ጸሎተ ቡራኬውንና አስተስርዮውን ከፈጸመ በኋላ «እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ» እንበል ይላል፤ ሕዝቡም ከካህኑ ጋር ፲፪ ጊዜ «እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ» ፲፪ ጊዜ «በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ» ይላሉ ።

ረ. ከዚህ ቀጥሎ ካህኑ «እግዚአብሔር የሀሉ ምስለ ኵልክሙ» ይላል ፤ ሕዝቡ «ምስለ መንፈስከ» ይሉና «አሜን እግዚአብሔር ይባርከነ ለእግብርቲሁ በሰላም» ብሎ «ኪያከ እግዚኦ ነአኵት ነሚአነ ጸጋ ዘእመንፈስ ቅዱስ» እስከሚል ድረስ ያለውን የመጨረሻ ጸሎት በኅብረት ይጸልያሉ ።



ሰ. ቀጥሎ ዲያቆኑ «ዕትዉ በሰላም» ብሎ ያሰናብታል ፤ ሕዝቡም ካህናቱም የሠራዒውን ካህን እጅ እየተሳለሙ ይሄዳሉ ።

ቀ. ካህኑ ቀሳውስቱን ሲያሳልም «ሢመተ እዴሁ ለአቡነ ጴጥሮስ» ይላል እነሱም«እግዚአብሔር ይሢምከ ውስተ ዘለዓለም መንግሥቱ» እያሉ መልስ ይሰጡታል ።

ዲያቆናትን ሲባርክ «እግዚአብሔር ልዑል ይባርከ ወያብርህ አዕይንተ አልባቢከ» እያለ በእጁ ይባርካል፤ ሕዝቡን በሚባርክበት ጊዜ ወንዶችን «እግዚአብሔር ልዑል ይባርከ ወያርኢ ገጾ ላዕሌከ» እያለ ይባርካል ፤ ሴቶችን ሲባርክ «እግዚአብሔር ልዑል ይባርኪ ወያርኢ ገጾ ላዕሌኪ» እያለ ይባርካል ፤ ከዚህ በኋላ እንደ ቅዳሴው ሥርዓት ንፍቅ ካህን ጸሎተ አውሎግያን ይፈጽማል ።

## ንስሐና ኑዛዜ

ንስሓ የግእዝ ቃል ነው ትርጕሙ በሠሩት ኃጢአት መጸጸት ወደ ገቢረ ኃጢአት አለመመለስ ነው ኑዛዜንም ለማግኘት ኃጢአትን ለመምህረ ንስሓ መናገር ነው ።

ሰው በሠራው ኃጢአት ተጸጽቶ ኃጢአቱ ይሰረይለት ዘንድ እግዚአብሔርን በኃዘን በልቅሶ ይቅር

www.ethiopianorthodox.org

ወደ ካህን የሔደ ተነሳሒ ሲታወቀው በድፍረት ሳይታወቀው በስሕተት የሠራውን ገልጦ ሲናገር ካህኑ ቀኖና ይሰጠዋል ። የሠራውን ኃጢአት የፈጸመውን በደል ገልጦ ካልተናገረና ከአልተጸጸተ በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም» እንደተባለው ፍጹም ድኅነትን ሊያገኝ አይችልም ።

ስለዚህ ከልብ መመለስ ባለፈው ኃጢአት መጸጸትና ይህን ከመሰለው ኃጢአት ለመጠበቅ ቁርጥ አሳብ ማድረግ ንስሓ ይባላል ።

ካህኑ ንስሓውን ተመልክቶ በሰፊሐ እድ በስቂለ አዕይንት በአንቃዕድዎ ሕሊና የንስሓ ጸሎት ኑዛዜ ከአደረገለት በኋላ ተነሳሒውን ፍትሐት ሰጥቶ (እግዚአብሔር ይፍታህ ብሎ) ያሰናብተዋል ።

በዚህ ጊዜ ተነሳሒው ስርየተ ኃጢአት ያገኛል፤እግዚአብሔር ሰውን ከመውደቅ የተነሣ አንዱ እንኳ እንዳይጠፋ የበደለውን ሁሉ ይቅር ለማለት ታላቁን የምሕረት በር ንስሓን ከፈተ ይህም ምሥጢር ያለማቋረጥ እንዲሠራ ሥልጣኑን ለሐዋርያት ሰጠ ።

«የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ እሰጥሃለሁ በምድር ያሠርኸው በሰማይ የታሠረ ይሆናል በምድርም የፈታኸው በሰማይ የተፈታ ይሆናል» እንዳለ ማቴዎስ ፲፮ ・ ፲፱ ・ ፲፰/፲፰።

ካህናት የሕይወት መሰላል ወይም ድልድይ ሆነው የሕዝቡን ንስሓና ልመና ወደ እግዚአብሔር ፣ የእግዚአብሔርን ምሕረት ወደ ሕዝቡ የሚያደርሱ



ናቸው ፤ በኃጢአት የሚሰናከል ሁሉ ንስሓ ያስፈልገዋል ንስሓ ዘማዊውን እንደ ድንግል ፣ ኃጢአተኛውን እንደ ጻድቅ ያደርገዋል በአንብዐ ንስሓ መታጠብ ፍጹም ንጹሕ ያደርጋል፤ የንስሓ ጥምቀት በዕንባ መታጠብ ነውና ይህም ነቢዩ ዳዊት«ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን በዕንባዬ አጥባለሁ ምንጣፌንም በዕንባዬ አርሳለሁ» እንዳለው ነው። (መዝሙር ፮.፮.)

## ሥርዓተ ንስሓ

በንስሓ የሚሰጠው ቀኖና በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ይፈጸማል ተነሳሒው ኃጢአቱን ለመምህረ ንሥሓው ይነግረዋል መምህረ ንስሐው የተነሳሒውን ዐቅም መዝና የጾም የጸሎት የስግደት የምጽዋት ቅጣት ይሰጠዋል ፤ ለዚህም ጊዜ ይወስንለታል ፤ የቀኖናውን ጊዜ ከጨረሰ በኋላ ተነሳሒው ወደ መምህረ ንስሐው ተመልሶ እንደትእዛዙ መፈጸሙን ይነግረዋል ቄሱም ፍትሐት ሰጥቶ (ናዝዞ) ሥጋውን ደሙን አቀብሎ ከምእመናን ጋር እንዲቀላቀል ይፈቅድለታል የንስሓ ሥርዓት ይህ ነው ።

## የክህነት አመሠራረት

ክህነት የተጀመረ በመጀመሪያው ሰው በአዳም ነው እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ፈጥሮ በልጅነት አከብሮ ነቢይ ካህን አድርጎ ስለሾመው በእሪት ፣ በወንጌል ሥርዓት እስኪወሰን ድረስ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ የነበሩ አበው በበረከት አበው

www.ethiopianorthodox.org

ከእግዚአብሔር እየተሾሙ ትንቢትን፣ ክህነትንከ ቅዱስ መንፈሱ እየተቀበሉ (እየተሾሙ)፣ በነቢይነታቸው ያለፈውን የሚመጣውን ሲገልጡ ሲያስተምሩ፣ በክህነታቸው መሥዋዕት ሲያቀርቡ፣ በጸሎታቸው አምላካቸውን ሲጠሩና ቃል በቃል ሲነጋገሩ ኖረዋል

አዳም ከገነት በወጣ በማግሥቱ በሠራው ኃጢአት ተጸጽቶ እያዘነና እያለቀሰ ቸርነት ምሕረት የባሕርዩ ከሆነው አምላክ ምሕረት ለመጠየቅ የመዓዛ መሥዋዕት አቀረበ ።

«ወዐጠነ አዳም ምስለ ትንሣኤ ፀሐይ በከርቤ ወሜዓ ወሰሊክ» (ኩፋሌ ፭.፩—፭)

## ምሥጢረ ክህነት

ምሥጢረ ክህነት ክፍ ያለ ምሥጢር ነው የማሠር የመፍታት ሥልጣን ያለው ሌሎችንም የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ለመቀደስ ለማክበር ለመፈጸም ችሎታ ያለው ክርስቶስ የመሠረተው የሠራው ከእርሱም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያለማቋረጥ የሚሰጥ ጸጋ ነው፤ ይህንንም ሥልጣን ክርስቶስ ለሐዋርያት በንፍሐት በአንብሮተ እድ ሰጥቶዋቸዋል፤ዮሐንስ ፳. ፳፩ና ፳፫፤ ሉቃስ ፳፬. ፵፤ ሐዋርያትም ለተከታዮቻቸው በአንብሮተ እድ እያስተላለፉ እስከ ዛሬ ደርሰዋል ።

ማስረጃ የሐዋርያት ሥራ ፮.፫—፮ ፡ ፲፬.፳፫ ፩. ጢሞቴዎስ ፬.፲፬.፤፪ኛ ጢሞቴዎስ ፩.፮.፤ ቲቶ፩.፭ እስከ ምጽአትም እንዲሁ ያለማቋረጥ እንደሚ



ሰጥ የተረጋገጠ ነው፤ ለምሥጢረ ክህነት የሚታይ አገልግሎት የማይታይ ሀብት አለው፤ የሚታየው አገልግሎት ጳጳሱ በአንብሮተ እድ ሲሾም የተለየ ጸሎት ሲጸልይ ክህነት የሚቀበለውም በሰቂለ ሕሊና በሰፌሐ እድ በአንቃዕድዎ አዕይንት በአድንኖ በተመስጦ ሲጸልይ ይታያል ፤ ይህ የሚታይ አገልግሎት ይባላል፤ ሆኖም ሥልጣነ ክህነት ጸጋ ሀብት የማሠር የመፍታት የማንጻትና የማጽናት የማዳን ሥልጣን ሲሰጥ አይታይም፤ ይህ የማይታይ ሀብት ይባላል ፤ ክህነት ለሁሉ አይሰጥም በምእመናን ለተመረጡ ሰዎች ብቻ ነው፤ ሢመተ ክህነት አይደገምም በየደረጃው አንድ ጊዜ ብቻ ነው ሹመቱ የሚሰጠውከፈረሰይቀራል፤አይታደስምአ ይጠገንም።

## የክህነት ተግባር

እግዚአብሔርንና ሰውን ማገልገል ነው እግዚአብሔርን ማገልገል ማለት ካህናት መላእክትን መስለው በመዓልትና በሌሊትም ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምስጋና ነው ፤ ሰውን ማገልገል ማለትም ማጥመቅ ማቍረብ መባረክ መናዘዝ በሞት ለሚለዩ ጸሎተ ፍትሐት ማድረግ በጠቅላላ በትምህርት በትሩፋት ክርስቶስን መስሎ አብነት ሆኖ መገኘት ነው ፤ ማቴዎስ ፲፫. ፩—፲፬ ፤ የሐ. ሥራ ፮.፬ ።

## ሢመተ ክህነት

ሢመተ ክህነት ፫ ደረጃ አለው ይኸውም ዲቁና ቅስና ኤጲስ ቆጶስነት ነው፤ከዚህም በላይ ጳጳስ ሊቀ

www.ethiopianorthodox.org

ጳጳስ ፓትርያርክ አለ ፤ እንደየማዕርጉም ሥርዓተ ሢመትና ጸሎት አለው ስለዚህም ሥርዓቱ እንዴት እንደሆነ ከአናጕንስጢስ እስከ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት በሕገ ቤተ ክርስቲያን የተወሰነው ሥርዓተ ሢመት በየደረጃው እንደሚከተለው ተገልጾአል ።

## ፩ኛ. የርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወይም የሊቀ ጳጳሳት አ፲፲ም ሥርዓት

ሀ. ሊቃነ ጳጳሳት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ ክርስቶስ የሾማቸው የሐዋርያት ተከታዮች ናቸው ። (የሐዋርያት ሥራ ፳.፳፰ ። )

ለ. በአንድ ዘመን በአንድ ወምበር ሁለት ሰዎች አይሾሙም ።

ሐ. ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሲሾም ሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳት ይገኛሉ፤ ይህ ሹመት ያለ ኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ አይደረግም ።

ማስረጃ «የሀልዉ ኤጲስ ቆጶሳት በሢመተ ሊቀ ጳጳሳት እስመ ኢይትፌጸም ዝንቱ ዘእንበለ በሀላዌ ጉባኤሆሙ ለኤጲስ ቆጶሳት ወሀላዌ ሜጥሮጶሊስ ዘውእቱ ጳጳስ» (ፍት.ነገ.አን.፬ ረስጣ ፩ ።)

## ፪ኛ. የኤጲስ ቆጶሳት ሢመተ ክህነት ሥርዓት

### ክፍል አንድ

ሀ. ኤጲስ ቆጶስ ኖላዊ (ጠባቂ) ነው (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭)



ለ. ኤጲስ ቆጶስነት የሚሾም ነውር የሌለበት በልቡናው ከሐኬት የነቃ የሚያረጋጋ እንግዳ መቀበልን የሚወድ የተማረ አብዝቶ የማይ ጠጣ ፈጥኖ የማይጣላ ብልህና ዐዋቂ ነው፤ «ወነዋ ይደሉ ከመ ይኩን ኤጲስ ቆጶስ ዘኢ ተረክበ ውስቴቱ ነውር ወዘአውሰበ አሐተ ብእሲተ ዘንቁሕ በሕሊናሁ ውእቱ ጠቢብ ወመናዝዝ ወመፍቀሬ ነግድ መምህር ዘኢያበ ዝኅ ስትየ ወይን ወዘኢያፈጥን እዴሁ ለዘቢጥ» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ፩ ጢሞ ፫ ፩-፲)

ሐ. ኤጲስ ቆጶስ በጠባዩ ትሑት የማይጣላ ትዕ ግሥተኛ ሰውን የሚያስታርቅ ገንዘብ የማይ ወድ ለሰው የሚያዝንና የሚራራ ቤቱ ሰቡን ሠርቶ ቀጥቶ የሚያኖር ልጆችን ሠርቶ ቀጥቶ የሚያሳድግ መክር አስተምሮ በንጽሕና እን ዲኖሩ የሚያደርጋቸው ሰካራምና ቁጡ ያል ሆነ ከቂም ከበቀል ከዓመፅ የተለየ ሐዲስ አማኒ ያልሆነ እንዲሆን ታዙዋል ፩ ጢሞቴ ዎስ ፫. ፫-፯

መ. ኤጲስ ቆጶስ ዕድሜው ከ፶ ዓመት በታች የሆነ እንዳይሾም ተከልክሎዋል ። «ወዘኢኮነ ሕይወቱ ሕጹጸ እም ፶ ዓመት» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ድስቅ ፬ ።)

ሠ. ኤጲስ ቆጶስ በትምህርቱ ብሉይ ሐዲስ የተማረ ነገር ዐዋቂ እንዲሆን ታዙዋል ።

ረ. ኤጲስ ቆጶስ የሚሆነው ምንኵስና ያለው ነው (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ። )

www.ethiopianorthodox.org

ሰ. ኤጲስ ቆጶሱን የሚመርጡት ፴ ዓመት የሆናቸው ናቸው (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ጠስ ፭፰ ።)

ቀ. ኤጲስ ቆጶስ የሚሾመው በሚሾምበት ሀገር ምእመናን ምርጫና በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ፈቃድ ነው (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭) «ለይሠየም ኤጲስ ቆጶስ በኅርየተ ኵሎሙ ሕዝበ ዚአሁ በሥምረተ መንፈስ ቅዱስ» (ፍትሐ ነገሥት ፭ ድስቅ ፴፮ ።)

«እመቦ ብእሲ ዘአምጽእዎ ከመ ይሠየም ኤጲስ ቆጶስ ወይኩን ዝንቱ በሥምረተ ሰብአ ብሔሩ ኵሎሙ ወይኩን ዝንቱ ጳጳሰ አው ሊቀ ጳጳሳት ዘይሠየም - --» (ፍትሐ ነገሥት ፭ ረስጣ፪ ።)

በ. ካህናቱና ሕዝቡ እንዲሾምላቸው ኤጲስ ቆጶስ የሚሆነውን ቆሞስ መርጠው ሲያቀርቡ ስለ ደግነቱና ትሩፋቱ ስለ ንጽሕናውና ከነውር የራቀ ስለመሆኑ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ፫ ጊዜ እየመላለሰ ማረጋገጫ ይጠይቃቸዋል፤ሕዝቡም አረጋግጠው የሚገባው ነው ብለው ፫ ጊዜ መልስይሰጣሉ፤ በ፫ኛው ሕዝቡ መልስ ሲሰጡ እጃቸውን አንሥተው ይገባዋል እያሉ ያጨ በጭባሉ (ፍት . ነገ . አንቀጽ ፭ ረስጠብ ፶፪።)

ተ. በሹመቱ ጊዜ ፫ ወይም ፪ ኤጲስ ቆጳሳት ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ጋር አብረው ይሾማሉ አንብሮተ እድ ያደርጋሉ ።

«ወየሐልዉ ለሢመተ ኤጲስ ቆጶሳት ክል ኤቱ አው ሠለስቱ እስመ ዝንቱ ውእቱ ዘይዌስክ



ሞገሶ» ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ረስጠ ፪ ።
«ወየሀልዉ ከመ ይሢምዎ ክልኤቱ ኤጲስ ቆጶሳት አው ሠለስቱ» ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ረስጠጅ ፩ ።

ኀ. ደግነቱ ያልታወቀ በራሱ ፈቃድ ዐባለ ዘሩን የሰለበ ቀድሞ ሳያምን ኑሮ ኋላ የተጠመቀ ኃጢአተኛ ሁኖ ኖሮ በኋላ ንስሓ የገባ ኤጲስ ቆጶስነት አይሾምም ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ረስጠጅ ፩፭ ።

ነ. ምንም ቢሆን ኤጲስ ቆጶስ በአንድ ኤጲስ ቆጶስ አይሾምም ፤
ማስረጃ «ወኢይደሉ ከመ ይሠየም ለክሙ እም አሐዱ ኤጲስ ቆጶስ እስመ ስምዓ ክልኤቱ አው ሠለስቱ ይከውን ቀዋሚ - - - - ለእመ ኮነ ውእቱ ኤጲስ ቆጶስ አሐዱ ዘአንበረ እዴሁ ላዕሌሁ ይትፈለጥ» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ረስጣ ፶፰ ድስቅ ፴፬) ።

አ. አንድ ዓይናና አንካሳ ኤጲስ ቆጶስነት ከመ ሾም አይከለከልም ፤ ይኸውም አንካሳው ዘሮ የሚያጥን ዐውድ የማይጥል ፡ አንድ ዓይናው ቀለም የማይጥል ፍታቴ የሚያደላድል ከሆነ ነው ።

ማስረጃ ፤ «ወኢይትከላዕ ከመ ይኩን ኤጲስ ቆጶሰ ነቋር ወኢሐንካስ ለእመ ኮነ ይሜኒ ለዝ ግብር»(ፍትሐ ነገሥትአንቀጽ ፭ ረስጠጅ ፩፪)

ከ. ኤጲስ ቆጶስ የሚሾመው እሑድ ነው ተሿሚውን በሚገባው ወምበር ያስቀምጡታል ። ማስረጃ « ወይሠየም ኤጲስ ቆጶስ በዕለተ እሑድ»(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ድስቅ ፴፯) ።

ወ. ኤጲስ ቆጶስ ሲሾም ካህናቱም ሕዝቡም በሙሉ ተገኝተው እየመሰከሩለት ነው የሚሾመው ። ማስረጃ «ወኵሎሙ ሰብእ ይንበሩ በእንተ ተሠይሞቱ ሕዝብኒ ወካህናት እንዘ ስምዐ ይከውኑ ሎቱ»(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ።)

ዐ. በአንብሮተ እድ ኤጲስ ቆጶሱን ሲሾሙ የተሰበሰቡ ኤጲስ ቆጶሳት እጃቸውን ይታጠባሉ ከታጠቡ በኋላ በአንብሮተ እድ ይሾሙታል ፤ ማስረጃ «ወኤጲስ ቆጶሳትኒ እለ መጽኡ ከመ ያንብሩ እደዊሆሙ ዲቤሁ ይትሐጸቡ እደዊሆሙ ወእምዝ ይሚምዎ»(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭) ።

ዘ. ኤጲስ ቆጶሳት በአንብሮተ እድ ሲሾሙት ሕዝቡ በፍርሃት ጸጥ ብለው ቆመው እጃቸውን ያነሣሉ ።

ማስረጃ

«ወሕዝብ ቀዊሞሙ በአርምሞ ወበፍርሃት ያንሥኡ እደዊሆሙ ወያንብሩ ኤጲስ ቆጶሳት እደዊሆሙ ዲቤሁ»(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭።)

የ. ኤጲስ ቆጶሳት በአንብሮተ እድ ሲሾሙ «ንሕነ ናንብር እደዊነ ዲበ ዝንቱ ገብር ኅሩይ ዘእግዚአብሔር በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ



ቅዱስ» እያሉ የቡራኬ ቃላት እየተናገሩ ነው ። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ።)

ደ. ኤጲስ ቆጶሳቱ የአንብሮተ እዱን ጸሎተ ቡራኬ ከፈጸሙ በኋላ ለተሿሚው መስቀል ይሰጡታል ፤ (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ።)

ገ. ኤጲስ ቆጶሳቱ በአንብሮተ እድ በሚሾሙበት ጊዜ በመጀመሪያ የተሾመው ኤጲስ ቆጶስ ከእለ ክርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ቀጥሎ በቅድሚያ አንብሮተ እድ ያደርጋል ። (እጁን በራሱ ላይ ይጭናል) ።

ማስረጃ «ወእምድኅረ ዝንቱ ያንብር ኤጲስ ቆጶስ ቀዳማዊ እምኔሆሙ እዴሁ ዲቤሁ » (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ።)

ጠ. ከዚህ በኋላ ጸሎተ ሢመቱን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ይጸልያል ፤ ሕዝቡ « አሜን» ይላሉ (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ።)

ፈ. ኤጲስ ቆጶሱ በተሾመ ጊዜ ሦስት ቀን በዓል ይከበራል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ።)

ፐ. ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመ በኋላ ሦስት ሱባኤ ይጾማል።የተሾመበት ወቅቱ በዓለ ሃምሳ ከሆነ በዚያ ጊዜ መጾም ስለማይቻል አሳልፎ በዚያው ዓመት በየሱባኤው ፫፡፫ ቀን ጾም ይጨርሳል ፤ ማስረጃ« ወእምከመ ተሠይመ ኤጲስ ቆጶስ ይንበር ሠለስተ ሱባኤያተ በጾም ዝንቱ ለእመ ኢኮነ በመዋዕለ ሃምሳ» (ድስቅ ፴፫) ፤

www.ethiopianorthodox.org

- - - «ወእምዝኒ ይፈጽም ይእተ ዓመተ በበሠለስቱ»(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳ ። )

ሀ. ምክንያት ከአልከለከለው በስተቀር ዕለት ዕለት ሥጋወን ደሙን ይቀበል ዘንድ መትጋት አለበት ይህም በመላ ዘመኑ ጤነኛ ሁኖ ለመኖር እንዲረዳው ነው ።

ማስረጃ «ወይጽሐቅ ከመ ይትመጦ በኵሉ ዕለት ምሥጢራተ ለእመ ኢከልአ ምክንያት ከመ ይሕየው ባቲ በኵሉ ዘመን»(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳ ሥርዋጽ ፳ ።)

ለ. በማስተማር ጊዜ ንቁሕ ትጉሕ ዘወትር የሚያስተምር መጻሕፍትን የሚያነብብ ወንጌልን አሪትን ነቢያትን መጻሕፍተ ሊቃውንትን ምዕራፉን ቍጥሩን አንቀጹን እየለየ የሚተረጕም እንዲሆን ታዞዋል(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳ ።)

ሐ. ኤጲስ ቆጶስ በሃይማኖት ወደ ማይመስሉ ወደ አሕዛብ በዓል እንዳይሔድና እንዳያከብር ተከልክሎዋል ማስረጃ «ወኢይሑር ኀበ በዓላተ አሕዛብ»(ፍትሐ ነገሥት ፳ ።)

መ. ኤጲስ ቆጶስ ሕዝቡን በምሳሌነቱ ለማስተማር ማንንም የሚወድ የሁሉ ወዳጅ ቂም በቀል የማይዝ ኀዳጌ በቀል ልበ ሰፊ ነገር አላፊ መሆን አለበት ከማንኛውም መንፈሳዊ ሥራ ከአልሆነው የሰይጣን ሥራ ከሆነው ነገር ሁሉ መጠበቅ እንዳለበት ታዞዋል ። ነቢዩ ሆሴዕ«መምህሩ ደግ ከሆነ ሕዝቡም እንደሱ



ደጋግ ይሆናሉ»ብሎ እንደተናገረ ኤጲስ ቆጶሱ ደግ ከሆነ ብዙ ሰዎችን ወደርሱ መሳብ ስለሚችል ነው ።

«ወይኩን ፍቁረ ለኵሉ ወለኵሉ ግብር ሠናይ ዘሀሎ ላዕለ ሰብእ ለይርባሕ ለነፍሱ እስመ ኖላዊ ለእመ ርኅቀ እምዓመፃ ይስሕቦሙ ለአርዳኢሁ በከመ ይቤ ሆሴዕ ነቢይ እስመ በከመ ይከውን ካህን ከማሁ ካዕበ ሕዝብኒ» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳ ድስቅ አንቀጽ ፳ ሆሴ ፬፡ ፱ )

ሠ. ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ዘወትር ያገለግላል በመዓልትም በሌሊትም ስለራሱና ስለ ሕዝቡ ስለሀገሩና ስለዓለሙ ሁሉ ይጸልይ ዘንድ ታዞዋል ። በቤተ ክርስቲያን ብቻውን ይኖራል ማለት ቤቱን ከቤተ ክርስቲያን አጠገብ ያደርጋል ፤ ከአስፈለገው ፥ በጸሎተ ማኅበር የሚረዱትን አንድ ሰው ሁለት ሰው በቤቱ ለማኖር ይችላል ።

«ወለእመ ኮነ ሎቱ ዘያሠምሮ ለነቢር ምስሌሁ እመ አኮ አሐዱ አው ክልኤቱ ወውእቶሙ አሐቲ ነፍስ ምስሌሁ ይግበር በዘይትራድዕዎ በእንተ ዘይደሉ»(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ )፳ ።

ረ. ኤጲስ ቆጶስ ቀሳውስትን ይባርካል ፤ እሱ ግን በቀሳውስት አይባረክም ።

ማስረጃ «ኤጲስ ቆጶስ ይባርክ ወኢይባርክዎ ኪያሁ»(ፍትሐ ነገሥት ፳ ረስጠ ፳፩ ።)

www.ethiopianorthodox.org

ሰ. ኤጲስ ቆጶስ ከቀሳውስት እስከ ዐጸዌ ኖኅት ያለውን ሹመት ይሾማል ፤ ነገር ግን ሳይመ ረምር ሳይፈትን ማንንም ክህነት እንዳይሾም ተከልክሎዋል ።

ማስረጃ «ወኢታፍጥን አንብሮ እዴከ ላዕለ አሐዱሂ ወኢትሳተፍ በዝንቱ ኃጢአት ካዕበ» (፩ ጢሞ ፭ ፡ ፳፪ ፤ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፩ ክፍል ፬ ።)

ቀ. ከኤጲስ ቆጶሱ በስተቀር መሻር የሚገባውን ካህን ይሽራል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ክፍል ፬ ።

በ. እግዚአብሔር እንደ ሾመው ኖላዊነት በራሱ ብቻ ሳይሆን በሕዝቡም ኃጢአት ስለሚጠየቅ ተግቶ ማስተማርና ሕዝቡን ከኃጢአት መጠ በቅ እንዳለበት ታዞዋል ።

ማስረጃ«አንተሰ ጸርከ ጸረ ክቡደ ፥ ጽሑፍ ከመ እግዚአብሐር ይቤሎ ለሙሴ አንተ ወአሮን ትጸውሩ አበሳሆሙ ለሕዝብ - - - - - - ወሶበ መጽአ ኀቤከ ዘሀለዎ ቦቱ ዓቢይ አበሳ ኢትት ሐየይ ኪያሁ ይቤ ሕዝቅኤል በእንተ ኤጲስ ቆጶስ ዘይትሐየይ እንበይነ ሕዝቡ አሌ ሎሙ ለኖሎተ እሥራኤል እለ ኃደጉ አባግዒሆሙ ዘይ ርዕዩ ለአሐዱ አኮኑ አንትሙ ኖሎት ዘት ርዕዩ አባግዐ ወአንትሙ ለሀሊብ ትስትይዎ ወለጸምር ዘትለብስዎ ወለመግዝዕኒ ስቡሕ



ዘትጠብሕዎ ወአባግዐየሰ ኢትርዕዩ - - - ሕዝ ቅኤል»፴፬ ። ፩—፲፱ ።(አሪት . . . . ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ።)

ተ. ኤጲስ ቆጶስ ስሙ በጸሎት ላይ ይጠራል በቅ ዳሴም ይጠራል ፤ (ፍትሐ ነገሥት ፭ ክፍል ፬ ።)

ኀ. ኤጲስ ቆጶስ ሥጋውን ደሙን ከኤጲስ ቆጶ ሳት እንጂ ከቀሳውስት አይቀበልም ፤(ፍት፡ነገ፡ አን ፡ ፭ ፡ ክፍ ፡ ፬ ።)

ነ. ከካህናት መካከል እኔ በላይ ልቁም ልቀመጥ በማለት ጠብ ክርክር እንዳይሆን ካህናትም በመዓርግ ከሕዝቡ ጋር አንድ እንዳይሆኑ ሊቃነ ካህናት ከተራ ካህናት ጋር እኩል እንዳ ይሆኑ የካህናቱን ማዕርግና መቋሚያቸውን ማወ ቅና ጽፎ መያዝ እንደሚገባቸው ታዞዋል። «ወይደልዎ ከመ ይጽሐፍ ወያእምር ኵሎ ማዕር ጋተ ካህናት ወሥርዓታቲሆሙ ከመ ኢይኩን ማዕከሌሆሙ ጋዕዝ በዝንቱ ግብር ወከመ ኢይደ መሩ ሰብአ ቤተ ክርስቲያን እንተ ሐዋርያት ምስለ ሕዝባውያን በመዓርግ ወከመ ኢይኩኑ ምስለ ሊቃነ ካህናት በአምሳሊሆሙ»(የኒቅያ ሲኖዶስ አንቀጽ ፷፯ ።)

አ. ኤጲስ ቆጶስ የተሾመበትን መንበርና ሀገር ትቶ በሌላ ሀገር እንዲቀመጥ አልተፈቀደም ። ማስረጃ«ወኢይደልዎ ለኤጲስ ቆጶስ ከመ ይኅ ድግ መንበሮ ወይሑር ኀበ ካልዕ ሀገር»(፪ኛ ቀሌምንጦስ አንቀጽ ፲፩ ።)

www.ethiopianorthodox.org

ከ. ኤጲስ ቆጶስ የተሾመበትን ሀገር ለቆ ወደ ሌላ ሀገር መዛወር እንደ ሌለበት ባል ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ማግባት የማይገባውን ያህል አይገባውም ተብሎ ታዙዋል ። ነገር ግን ምክንያት ከተገኘበት ሊዛወር ይችላል ጥፋት ከሌለበት የሚዛወረው በዕድገት ነው ።

ማስረጃ«ወኢይሑር ኤጲስ ቆጶስ ኀበ ካልዕ ሀገር እምነ ሀገሩ ዘኮነ ላዕሌሁ ወተሠይመ ኤጲስ ቆጶስ በእንተ ረሓበ ብሔር ወናዕሰ ዚአሃ ወውኀደተ ሰብእ ወበረከታቲሃ ወዝን ቱሰ ይትሜሰል አምሳለ እለ አውሰቡ ብእሲተ እምነ ሕዝባውያን ለእመ ተአቅፈ ብእሲ በብ እሲቱ ዘእንበለ በምክንያተ ዝሙት ለእመ ፈቀደ ወልጦታ በዘትሤኒ እምኔሃ ውእቱ መዓ ብስ ፈድፋደ ወከማሁ ኤጲስ ቆጶስኒ ወካህ ናት አምሳለ እለ የሐሥሡ ፈድፋደ ዘይኄይስ እምሀገሮሙ» (ጉባኤ ኒቅያ ፳፯)

ወ. ኤጲስ ቆጶስ ቢያጠፋ ባላመኑ ሰዎች ምስክ ርነት ወይም የአንድ ኤጲስ ቆጶስ ምስክርነት አይሰማበትም ፤ ማስረጃ «ኢይትወከፉ ስምዐ ሐራጥቃ ዘውእቶሙ ዓላውያን ላዕለ ኤጲስ ቆጶስ» (፫ኛ/ ቀሌምጦስ አንቀጽ ፸ ።)

«ወኢይትወከፍ ላዕሌሁ ስምዐ አሐዱ ኤጲስ ቆጶስ» ፪ኛ ቀሌምንጦስ ፲፪»



## ክፍል ሁለት

### ሁለተኛው ክፍል የኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ ሥነ ሥርዓት ነው

ሀ. ኤጲስ ቆጶሳት በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባሉ ማስረጃ «ወይኩን ጉባኤ ኤጲስ ቆጶሳት ክል ኤተ ጊዜ በበዓመት »(ፍትሐነገሥት አንቀጽ ፭ ክፍል ፩ ረስጠብ ፳፺ ረስጠጅ ፳፫ ጾክ፳፫)

ለ. የመጀመሪያው ጉባኤ በበዓለ ፶ በ፬ኛው ሱባኤ በአራተኛው ቀን ይደረጋል፤ ይኸውም ርክበ ካህናት በሚውልበት ቀን ማለት ነው ፤ ሁለተኛው ጉባኤ ጥቅምት በባተ በ፲፪ኛው ቀን ይደረጋል፤ይህም ዕለት ዕለተ ዕረፍቱ ለማ ቴዎስ ወንጌላዊ ነው ።

ማስረጃ «ወጊዜ ቀዳሚት ጉባኤ በራብዕ ሱባኤ እምሃምሳ ወዳግሚትኒ አመ ፲ ወ፪ ለጥቅምት» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ክፍል ፩) «ይት ጋብኡ ኤጲስ ቆጶሳት ዘኵሉ መካናት ኀበ ጳጳሶሙ አው ኀበ ሊቃነ ጳጳሳቲሆሙ ክልኤተ ጊዜ በኵሉ ዓመታት» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ኒቅያ ፴ ፤ ፵፭።)

ሐ. በጉባኤው መካከል አንድ መንበር ተደርጎ በላዩ ላይ ወንጌል ይቀመጣል፤ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በፊት ለፊት ይቀመጣሉ፤ በር ይዘጋና ኤጲስ ቆጶሳት ተነሥተው የማኅበር ጸሎት ያደርጋሉ፤ ጸሎቱ ሲያልቅ ይቀመጣሉ ከዚያ በኋላ ስለ ሃይማኖት መጽናት ስለበጎ ምግባር

www.ethiopianorthodox.org

መስፋፋት ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መቃናት በጠቅላላው ስለመንፈሳዊ ሕግና ፍትሕ ተነጋግረው ውሳኔ ይሰጣሉ ።

ማስረጃ «ወያንብሩ ማዕከለ ምርፋቆሙ አሐደ መንበረ ወያንብርዎ ዲቤሁ ለወንጌል ቅዱስ ወይንበር ሊቀ ጳጳሳት በቅድሜሆሙ ወይዕጽዉ አናቅጸ ወይትነሥኡ ኅቡረ ወይጸልዩ ወይግብኡ ኀበ ምርፋቆሙ ወይኅትቱ በእንተ ግብር ዘተጋብኡ በእንቲአሁ በኅቡዕ» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ክፍል ፭ ።)

## ፫ የቅስና ሢመት ሥርዓት

### ፩. ለቅስና ሹመት የሚያበቁ ሁኔታዎች

ሀ. ለቅስና የሚመረጥ ዲያቆን ነውርና ነቀፋ የሌለበት አንዲት ድንግል ሴት ያገባ ደጎች ልጆች ያሉት ቂመኛ ያልሆነ አብዝቶ የማይጠጣ እጁን ለመማታት እንደበቱን ለመገዘት የማያፈጥን ገንዘብ የማይወድ እንግዳ መቀበልን የሚወድ በጎ ሥራን የሚያፈቅር ከኃጢአት የነጻ ደግና ቸር የሆነ ሰውነቱን ከፍትወት የገታ ወንጌልን በማስተማር ምእመናንን የሚረዳ እውነተኛ ትምህርት በማስተማር ሰውን ማጽናናት የሚቻለው ክደው ሊያስክዱ የሚተናኮሉትን የሚከራከራቸው መሆን እንደ አለበት ተሠርቷል ።

ማስረጃ ፡ (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፩ ዘሌ.፳፩.፯—፲፯)



ለ. ፴ ዓመት ያልሞላው ቅስና እንዳይሾም ተከልክሎዋል ።

ማስረጃ «ኢይሠየም ቀሲስ ዘእንበለ በ፴ዓመት» (ፍትሐ ነገሥት ፯ ቀጠግ ፲፩)

ሐ. ብሉያትን ሐዲሳትን ያልተማረ ይልቁንም አራቱን ወንጌል ያላወቀ ቅስና እንዳይሾም ተከልክሏል ።

ማስረጃ «ወኢይኩን አሐዱሂ ቀሲሰ ዘኢየአምር ነገረ መጻሕፍት አምላካውያት ሠናያት» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ በስ ፹፱)

መ. ለቅስና መብቃቱ ያልተመሰከረለት ቅስና አይሾምም ።

ማስረጃ «ወኢይኩን አሐዱሂ ቀሲሰ ዘኢተንዕደ በስምዐ ሃምስቱ ዕደው» (ፍትሐ ነገሥት ፯ በስ. ፵፯ ።)

## ፪ ሢመተ ቅስና

ሀ. ኤጲስ ቆጶስ ቄሱን በአንብሮተ እድ ይሾመዋል ቀሳውስት ቆመው ይዳስሱታል ይጸልዩለታል ቄስ ዲያቆን ንፍቅ ዲያቆንና ከዚያ በታች ያሉት የሚሾሙት በኤጲስ ቆጶስ ብቻ ነው ኤጲስ ቆጶሱ እነዚህን ሲሾም የማዕርጋቸውንና የሥርዓተ ክህነታቸውን ደረጃ ጠብቆ በሕዝብ ፊት ጸሎተ ሢመቱን አድርሶ ይሾማቸዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ማስረጃ «ወለእመ ፈቀደ ኤጲስ ቆጶስ ከመ ይሢም ቀሲሰ ያንብር እዴሁ ላዕለ ርእሱ ወቀሳውስትኒ ዙሎሙ ይግሥሥዎ ቀዊሞሙ ወይጸልዩ ላዕሌሁ» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ
፮ ክፍል ፪ ረስጠ ፳፪፥፵፬ ።)

ኤጲስ ቆጶስ ሳይፈቅድ ቄስና ዲያቆን አይሾሙም ፤ ማስረጃ «ወኢይሠየም ቀሲስ አው ዲያቆን ዘእንበለ በምክረ ኤጲስ ቆጶስ ዘውእቶሙ ታኅተ ሥልጣኑ ወይሢም ኤጲስ ቆጶስ ባሕቲቱ እስመ ሣልሳይ መዓርጊሁ» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፮)

ክፍል ፪.በስ ፲ ረስጠ ፪ ።

## ፫. የቀሳውስት ተግባርና ሥልጣን

ሀ. ቄስ መምህር ነው መምህርም እንደመሆኑ የቀናች ሃይማኖትን ያስተምራል ።
ማስረጃ «እስመ ቀሲስ በአምሳለ መምህር ወይኩኑ ቀሳውስት በኀቤክሙ መምህራነ ለአእምሮተ እግዚአብሔር» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፮ ድስቅ ፳፮ )

ለ. ቄስ ሥራው ማስተማር ማጥመቅ ፣ ቅድሶ ማቁረብ ፣ መባረክ ፣ ማሠርና መፍታት ማናዘዝ ነው ።

ማስረጃ (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፮ ክፍል ፫.



ሐ. ቄሱ በአንብሮተ እድ ሕዝቡን ይባርካል ማስረጃ «ወይባርክ ወኢይትባረክ እምዘውእቱ ይንዕስ» ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፮ ረስጣ ፶፰)

መ. (ቄስ ሥልጣነ ክህነት አይሾምም አይሽርም (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፮ ክፍል ፫)

## ፬ ትእዛዘ ቀሳውስት

ሀ. ቄስ ምእመናንን መጠበቅና ሲታመሙ መጎብኘት በትምህርት ማጽናት እንደሚገባው ታዞዋል እውነተኛ ፍርድም መፍረድ ይገባዋል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፮ ክፍል ፬። )

ለ. በመሠዊያው ቀኝ የሚቆሙ ቀሳውስት ኅብስቱን ያስተናብራሉ ፤ ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉትን በየተራቸው እንዲቀበሉ ይቈጣጠራሉ ፤ በግራ የሚቆሙ ቀሳውስት ሕዝቡን ያስተናብራሉ ።

ማስረጃ «ወቀሳውስት እለ ውስተ የማን ያስተሐምሙ ለረድኤት በውስተ ምሥዋዕ ከመ ያክብርዎ ለዘይደልዎ ክብር ወይመንንዎ ለዘይደልዎ ምናኔ ወቀሳውስትሰ እለ ውስተ ጸጋም ያስተሐምሙ በእንተ ጉባኤ ከመ ይኩኑ ኅዱዓነ» (ፍትሐ ነገሥት ፮ ክፍል ፬ ።)

ሐ. ቀሳውስት ሐዋርያት ከሠሩት ሥርዓት ውጭ ትእዛዝ በማክበድ ሕዝቡን እንዳያስጨንቁ ታዞዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ማስረጃ«ወኢይወስክ አሐዱ እምቀሳውስት ምንተኒ ክበደ ላዕለ ሕዝብ ውፁአ እምቀኖና አበዊነ ሐዋርያት» (ፍትሐ ነገሥት አግቀጽ ፯ በሰ.፺፭ ።)

መ. ቄስ ታሞ በሚመረመርበት በሚታከምበት ጊዜ ከአልሆነ በስተቀር በማንም ፊት ፈጽሞ ዕርቃኑን ሊጥልና ሊጋለጥ አይገባውም ። ማስረጃ ወኢይትአረቅ ቀሲስ ግሙራ ቅድመ መኑሂ እምሰብእ ዘእንበለ በጊዜ ዐጸባ (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፩.በስ ፺፫ ።)

ሠ. ቀሳውስት ከኤጲስ ቆጶሱ ዘንድ በየዓመቱ ፫ ጊዜ እንዲሰበሰቡ ታዘዋል ። ማስረጃ «ወይትጋብኡ ቀሳውስት ኀበ ኤጲስ ቆጶሳቲሆሙ ሠለስተ ጊዜያተ በበዓመት (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፩.ኒቅያ ፺፱) ።)

ረ. ካህናት የራስ ጠጕራቸውን ማሳደግና ማጎፈር አይገባቸውም ።

## ክፍል አምስት

## ቀሳውስት ከሹመት የሚሻሩበት ሥርዓት

ሀ. በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሊጠብቀው የታዘዘውን የማይጠብቅ፣ እንዳይሠራው የተከለከለውን የሚሠራ፣ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሕዝቡን የማያስተምርና የማይመራ ቄስ ሲኖር ከክህነቱ ይሻራል ።
(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፭ ።)



ለ. ቄስም ሆነ ዲያቆን ከሹመቱ በኃጢአት ከተሻረ በኋላ ደፍሮ ለአገልግሎት ቢገባ ከቤተ ክርስቲያን ተወግዞ ከምእመናን ይለያል እያወቀ በዚህ ድፍረቱ የተባበሩት ሁሉ ከምእመናን ይለያሉ ።

ማስረጃ ፤ (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ረስጠብ ፲፱ ጾክ ፬ ። )

ሐ. ቄስ ወይም ዲያቆን በሀገሩ የተሾመውን ኤጲስ ቆጶስን ንቆ አቃሎ ለብቻው ቤተ ክርስቲያን ከሠራ ኤጲስ ቆጶሱ እስከ ፫ ጊዜ ጠርቶት ከአልመጣ እሱና እሱን የመሰሉት ከሹመታቸው ይሻራሉ ፤(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ረስጠብ ፳፪ ።)

መ. ቄሱ ያለበትን ቤተ ክርስቲያን ትቶ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ከሔደ እንዲመለስ ተነግሮት ኮአልተመለሰ ከሹመቱ ይሻራል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ረስጣ ፲፬ - ኒቅያ ፲፬)

ሠ. ቄስ በቁጣ ወይም በማናቸውም ምክንያት ምእመናንን ሥጋ ወደሙ ከከለከለ ከሹመቱ ይሻራል ። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፭ ኒቅያ ፳፯ ። )

ረ. ቀሳውስት ዲያቆናት በሥጋዊ ነገር ዋስ ተያዥ ምስክር አይሆኑም ይህን ያደረገ ከሹመቱ ይሻራል(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፭ ኒቅያ ፳፰ ። )

www.ethiopianorthodox.org

## ፬. የዲያቆናት ሢመት ሥርዓት

### ክፍል አንድ

ሀ. ለዲቁና ሹመት የሚያበቁ ሁኔታዎች

ዲያቆናት ጭምቶች ትዕግሥተኞች ፣ ግብረ ገብነት ያላቸውና የሚታዘዙ ፣ ሁለት ቃል የማይናገሩ ማለት አንድ ጊዜ እውነት ፣ አንድ ጊዜ ሐሰት የማይናገሩ ፣ አብዝተው ወይን የማይጠጡ ፣ የማይገባ ትርፍ ገንዘብን መቀበል የማይሹ ፣ ንጹሕ በሆነ ልቡና ሃይማኖትን የተረዱ ፣ ጋብቻ ያልደገሙ ፣ ልጆቻቸውን ቤተሰቦቻቸውን ቀጥተው ፣ ሠርተው ያሳደጉ መሆን ይገባቸዋል ፤ በዚህ ሁሉ የተፈተኑና ነውር የሌለባቸው ሁነው ሲገኙ ዲቁና ይሾማሉ (፩ ጢሞ . ፫ ፰-፲፫(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ቀዳማዊ ጢት ፬ ።)

ለ. በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ለመዓርገ ዲቁና መብቃታቸው ተመስክሮላቸው እንዲሾሙ ታዞዋል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ረስጠ ፲፯ ።)

ሐ. ከዚህ ጋር ለሰው የሚራሩ ፣ የሚያዝኑ፣የማያንጐራጕሩ ፣ ከቂም ከበቀል የራቁ ቁጡዎች ፣ ብስጩዎች ያልሆኑ፣ የማያዳሉ ፣ ለመማርና ለማስተማር የተጉ እንዲሆኑ ታዝዘዋል ።
(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፭ ።)



### ክፍል ሁለት

#### ሢመተ ዲቁና

ሀ. ዲያቆን በአንብሮተ እድ ይሾማል

ማስረጃ«ስበ ትሠይሞ ለዲያቆን አንብር እዴከ ላዕሌሁ ወጸሊ» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ክፍል ፪ ረስጣ ፺፬ ቀጠግ ፺፬ ።)

ለ. ዲያቆናት ሲሾሙ ቀሳውስትና ዲያቆናት ከኤጲስ ቆጶሱ ጋር ሁነው አብረው ይጸልያሉ አንብሮተ እድ የሚያደርግለት ግን ኤጲስ ቆጶሱ ብቻ ነው ።

ማስረጃ « ወቀሳውስት ዙሎሙ ወዲያቆናትኒ እንዘ ይቀውሙ ይጸልዩ»(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፪ ረሰጣ ፺፬ ቀጠግ ፲፬ ።)

ሐ. ዲያቆን ፳፭ ዓመት ሳይሞላው አይሾምም ይላል ይሁን እንጂ ብቁ ሆኖ ከተገኘ ከዚህ ዕድሜ በታች ያለ ቢሆንም ይሾማል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፪ ቀጠግ ፲፭ ።)

መ. የዲያቆናቱ ቍጥር በቤተ ክርስቲያኑ ስበካ ስፋትና ጥበት ይወሰናል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ቀጠግ ፲፬ ኒቅያ ፳፯ ።

### ክፍል ፫

#### የዲያቆናት ሕይወትና ሥርዓት

ሀ. ዲያቆናት እንደ ኤጲስ ቆጶስ ፣ እንደ ቄስ ያለ ነውር ፣ ያለነቀፋ መኖር አለባቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ማስረጃ «ወይኩኑ ካዕበ ዲያቆናት ዘእንበለ ነውር በአምሳለ ኤጲስ ቆጶስ ወይኩኑ ፍጹማነ በክህነቶሙ ለቤተ ክርስቲያን በዘይክሉ ገቢረ ዘእንበለ ሐፍረት»(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፫ ድስቅ ፴፯ ።)

ለ. ዲያቆናት ለቦታው ሁሉ በመዓልትም በሌሊትም በጎ ሥራን የሚሠሩ መሆን ይገባቸዋል ። ከኃጢአት ንጹሕ ሁኖ መልካም አገልግሎትን የሚያገለግል ዲያቆን ይረባል ይጠቅማል በጎ ዕድል ፈንታን ያገኛል(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፬ ረስጣ ፲፰ ።)

ሐ. ዲያቆን የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደመሆኑ መጠን ለኤጲስ ቆጶሱና ለቄሱ ይላካል «ወዲያቆንሰ ከመ ዘይትለፀክ ለእግዚአብሔር ይትለዐክ ለኤጲስ ቆጶስ ወለቀሳውስት በኵሉ ግብር» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ በደስ ፳ ።)

መ. ዲያቆን ሕሙማንን በመጐብኘት የችግረኞችን ጉዳይ ወደ ቄሱ ወደ ኤጲስ ቆጶሱ በማቅረብ ለችግረኞች ምጽዋት የሚሰጡትን ምእመናንን ሁሉ በማስተባበርና በመላላክ እንዲያገለግል ታዝዞአል፤(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፫ ።)

ሠ. ዲያቆን በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ ሕዝቡን ሥርዓት ይዘው እንዲቆሙና እንዲጸልዩ እንዳያንቀላፉና እንዳይተኙ እንዳይስቁና እንዳይሳለቁ ይቈጣጠራል(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፲፪ ድስቅ ፲፪ ።)



ረ. ሥጋውን ደሙን በማቀበል ጊዜ ሥጋውን ቄሱ ሲያቀብል ደሙን ዲያቆን ለሕዝብ ያቀብላል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፫ ረስጠ ፶፰ ።)

ሰ. ቆሞሱና ሊቀ ዲያቆናቱ ለኤጲስ ቆጶሱ እንደ ሁለት እጆችና እንደ ሁለት ክንፎች ሆነው ሹመት በሚሰጥበት ጊዜ በቀኙና በግራው ይቆማሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሔድ አብረው ይሔዳሉ ወደ ሌላም ቦታ ሲሔድ አይለዩም ሊቀ ዲያቆናት በቀኙ ይቆማል ሌሎች ግን በግራ ይቆማሉ ።

ማስረጃ « ወኮሮአቢ ስኒ ይኩን ከመ ክልኤ እደዊሁ ወክልኤ ክነፊሁ ለኤጲስ ቆጶስ ወሶበ የሐውር ኀበ ቤተ ክርስቲያን አው ኀበ ካልዕ ይደሉ ከመ ይኩን ሊቀ ዲያቆን በየማኑ ወካልዐንሂ በጸጋሙ» (ፍትሐ ነገሥት ፯ ኒቅያ ፳፪)

## ክፍል ፬

## ዲያቆን ከመዓርጉ የሚሻርበት ምክንያት

ጉቦ ሰጥቶ የተሾመ፥ ወይም በጉልበት አስገድዶና አስፈራርቶ የተሾመ ፥ወይም በተንኮል የተሾመ፥ ወይም ሁለት ጊዜ የተሾመ፥ ሁለት ሴት ያገባ፥ በተሾመ ጊዜ ከሴት ርቄ ንጽሕ ጠብቄ እኖራለሁ

www.ethiopianorthodox.org

ብሎ ተሥሎ ከተሾመ በኋላ ስዕለቱን አፍርሶ ሚስት ያገባ ፣ ዘወትር የሚሰክር፣በክፉ ሥራ ጸንቶ የሚኖር ፣ በሐሰት የሚመሰክር፣አራጣ የሚቀበል፣ባልንጀራውን የሚያማ፣ በሰው የሚታበይ፣ ኃይልን የሚያሳይ፣ከዘማዊት ሴት የደረሰ፣ ቤተ ክርስቲያኑን ትቶ ከሔደ በኋላ የተመለሰ፣ ኤጲስ ቆጶስ ሳይፈቅድለት የመነኰሰ፣ ተደብቆ ተክሊል ያደረሰ ፣ ሰውን የሚመታ ፣ እመነኰሳለሁ፣ ተባሕትዎ እይዛለሁ ብሎ ሚስቱን የፈታ፣ ከመናፍቃን የተጠመቀ ፣ ቍርባናቸውን የተቀበለ ፣ ኤጲስ ቆጶሱን የናቀና ያቃለለ ፣ ከመናፍቃን ጋር የጸለየ፣ ከተሻረ በኋላ የክህነት ሥራ የሚሠራ ፣ ለብቻው ሌላ ቤተ ክርስቲያን የሠራ፣ ኤጲስ ቆጶሱ ጠርቶት አልመጣም ብሎ የቀረ፣ ቤተ ክርስቲያኑን ትቶ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን የሔደ፣ ወደ ንግድ የሔደ፣ከደሟ ያልነጻችውን ሴት ከቤተ ክርስቲያን ያስገባ፣ ሥጋወደሙን ያሰጠ ፣ ከዲቁናው ማዕርግ ይሻራል። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፩ ።)

## ፩. የንፍቅ ዲያቆናት ሢመተ ክህነት ሥርዓት

## ክፍል ፩

## ለንፍቀ ዲቁና ሹመት የሚያበቁ ሁኔታዎች

ነገር የማያበዛ ፣ የማይሰክር ፣ ዋዛ ፈዛዛ የማይናገር ፣ በጎ አኗኗር ያለው ፣በጎ ነገርን የሚወድ፣የሃይማኖት ትምህርት ወደ ሚሰጥበት ጉባኤ የሚሔድ፣ ታዛዥ የሆነ ንፍቀ ዲቁና ይሾማል(ፍትሐ ነገሥት ፭. ረስጣ ፲፩ ።)



## ክፍል ፪

## ሥርዓተ ሢመተ ንፍቀ ዲያቆናት

ሀ. ኤጲስ ቆጶስ ንፍቀ ዲያቆኑን ሲሾም አንብሮተ እድ አያደርግም በቃል ብቻ ንፍቅ ዲያቆን ብሎ ይሰይመዋል ።(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ክፍል ፪ ረስጣ ፳፯ ።)

ለ. ንፍቅ ዲያቆን ሚስት ያላገባ ከሆነ ከሴት ርቆ ንጽሕ ጠብቆ እንዳኖረ ከአልተመሠከረለት አይሾምም ።(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ክፍል ፪) ።

## ክፍል ፫

## የንፍቀ ዲያቆናት ሥራ

ሀ. ንፍቅ ዲያቆናት ዲያቆናትን ይረዳሉ ፤

ማስረጃ «ንፍቀ ዲያቆናትሰ ከመ እንተ ረዳእያን» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ክፍል ፫ ።)

ለ. ንፍቀ ዲያቆናት በዲያቆናት ቦታ ገብተው በዲቁና መዓርግ ማገልገል ንዋየ ቅድሳት መንካት የዲያቆናትን ልብሰ ተክህኖ መልበስ አይችሉም። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ክፍል ፫ ጾክ ፵፭ ፵፮/፵፯/ ፳፯ ፷፩/፷፪/፷፫/፵፫ ።)

ሐ. ንፍቀ ዲያቆን በመቅደሱ በር ከውጭ ይቆማል ከዚያ አይለይም) ፍትሐ ነገሥት ፭/፫ ።

መ. ንፍቀ ዲያቆን ደሙን አያቀብልም ። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ክፍል ፫ ጾክ ፴፪)

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፬

## ንፍቀ ዲያቆን የሚሻርበት ምክንያት

ንፍቅ ዲያቆን ከሰረቀ አንድ ዓመት ከሹመቱና ከሥራው ይታገዳል ከዓመት በኋላ ወደ ሥራው ይመለሳል ወደ ዲቁና ማዕርግ አይደርስም እስከ ዕለተ ሞቱ በንፍቀ ዲቁና ማዕርግ ይኖራል ።(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፫ ክፍል ፬ በስ ፵፫ ።)

## ፲፮ የአናጕንስጢስ ሢመት ሥርዓት

## ክፍል አንድ

## ለአናጕንስጢስ ሹመት የሚያበቃ ሁኔታ

አናጕንስጢስ ማለት አንባቢ ማለት ነው በችሎታው፣ በበጎ ጠባዩ የታወቀ፣ ነገር የማያበዛ፣የማይሰክር፣ ዋዛ ፈዛዛ የማይናገር በጎ አኑዋኑዋር ያለው፣ በጎ ነገርን የሚወድ፣የሃይማኖት ትምህርት ወደ ሚሰጥበት ጉባኤ ለመሔድ የሚፋጠን፣ ታዛዥ የሚያነብበውን ለመሥራት የሚተጋ፣የሚያነብበውን ኃይለ ቃል የሚያውቅ አናጕንስጢስነት ይሾማል።(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፫ ክፍል ፭ ረስጣ ፲፭) ።

## ክፍል ፪

## ሥርዓተ ሢመተ አናጕንስጢስ

ሀ. አናጕንስጢስ በሚሾምበት ጊዜ አስቀድሞ ኤጲስ ቆጶሱ አንብብ ብሎ ወንጌል ይሰጠዋል፳። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፫ ክፍል ፪ ረስጣ ፳)



ለ. ኤጲስ ቆጶስ አናጕንስጢስን ሲሾም አንብሮተ እድ አያደርግም በቃል ብቻ አናጕንስጢስ ብሎ ይሾመዋል(ፍትሐ ነገሥት ፫ ፣ ክፍል ፪ ረስጣ ፳፯ በዶስ ፲ በስ ፵፫) ።

ሐ. አናጕንስጢስ ሚስት ያላገባ ከሆነ ከቤት ርቆ እንደ ኖረ ካልተመሰከረለት አይሾምም(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፫ ክፍል ፪) ።

## ክፍል ፫

## የአናጕንስጢስ ሥራ

ሀ. አናጕንስጢስ አንባቢ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን ያነብባል ( ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፫ ክፍል ፫ ድስቅ ቀዳማዊ )

ለ. አናጕንስጢስ ከፍ ካለ ቦታ ቆሞ ከብሉያት መጻሕፍት ሁሉ በክፍል በክፍል እየከፋፈለ እየመጠነ ያነብባል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፫ ክፍል ፫ ድስቅ ፲፪) ።

ሐ. አናጕንስጢሳውያን ንባብ በሚያነብቡበት ጊዜ ልብሰ ተክህኖ አይለብሱም ( ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፫ ክፍል ፫ )

## ክፍል ፬

## አናጕንስጢስ የሚሻርበት ምክንያት

ሀ. አናጕንስጢስ ከሰረቀ አንድ ዓመት ከሹመቱና ከማንበብ ሥራው ይታገዳል ፤ ከዓመት በኋላ

www.ethiopianorthodox.org

ግን ወደ ንባብ ሥራው ይመለሳል መዓርግ አይጨመርለትም እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በአ ንባቢነቱ ማዕርግ ይኖራል ።(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፰ ክፍል ፬ በስ ፵፰ ።)

ለ. በገና መች ኑሮ እንደሆነ ከተሾመ በኋላ ወደ ዚህ ሥራው መመለስ አይገባውም ከተመለሰና በዚሁ ሥራው ከተገኘ በሰባት ሱባዔ ጾም ይቀጣል ። ።

ከአልታረመ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይለያል(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፰፡ ክፍል ፬፡ በስ ፸፬ ።)

## ክፍል ፩

## ሥርዓተ አናጉንስጢስ

አናጉንስጢስ ሚስት ማግባት ይችላል፣ሚስቱ ከሞተችበት ሁለተኛ ያገባል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፰ ክፍል ፩ ረስጠብ ፲፩ በስ ፺፩)

## ፯ የመዘምራን ሥርዓት ሢመት

## ክፍል ፩

ኤጲስ ቆጶስ መዘምራንን በቡራኬ ይሾማል እንጂ አንብሮተ እድ አያደርግም(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፰ ክፍል ፪ )



## ክፍል ፪

## የመዘምራን ሥራ

ሀ. መዘምራን ዘማሪዎች ስለሆኑ ይዘምራሉ (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፰ ክፍል ፫ ድስቅ ፲፪ )

ለ. መዘምራን የሚዘምሩት ከመዝሙረ ዳዊት ነው ። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፰ ክፍል ፫ ድስቅ ፲፪) በሀገራችን የቅዱስ ያሬድን ድርሰት ጭምር ይዘምራሉ ።

ሐ. መዘምራን በሚዘምሩበት ጊዜ ልብሰ ተክህኖ አይለብሱም

«ወኢ ለአናጕንስጢሳውያን ወኢለመዘምራን ከመ ይልበሱ ሞጣሕተ ሶበ ያነብቡ («ፍትሐ ነገ ሥት አንቀጽ ፰ ክፍል ፫ ።)

## ክፍል ፫

## ሥርዓተ መዘምራን

መዘምራን ሚስት ማግባት ይችላሉ ሚስታ ቸው ከሞተችባቸው ሁለተኛ ማግባት ይች ላሉ(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፰ ክፍል ፩ ረስጠብ ፲፩ በስ ፺፩ )

www.ethiopianorthodox.org

## ሥርዓተ ዐጸውተ ኆዋኅው

### ክፍል ፩

### የዐጸውተ ኆዋኅው ሥራ

ሀ. ዐጸውተ ኆዋኅው (በር የሚከፍቱና የሚዘጉ) በወንዶች መግቢያ ቆመው ይጠብቃሉ
ማስረጃ «ወይቁሙ ዐጸውተ ኆዋኅው ካዕበ መካነ ሙባኢሙ ለእደው ወይፅቀብዎ»(ፍትሐነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፫ ድስቅ ፲፪)

ለ. ዐጸውተ ኆዋኅው አንዲት ሰዓት እንኳ ከበሩ መለየት የለባቸውም» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፫ ጾክ ፵፱ ።)

ሐ. ዐጸውተ ኆዋኅው ደሙን አያቀብሉም ። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፫ ጾክ ፴፱ ።)

መ. ዐጸውተ ኆዋኅው ሚስት ማግባት ይችላሉ ሚስቶቻቸው ከሞቱባቸውም ሁለተኛ ማግባት ይችላሉ፤(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፫ በስ፶፫)

## የዲያቆናውያት ሥርዓተ ሢመት

### ክፍል ፩

### ለዲያቆናዊት ነት ሢመት የሚያበቁ ሁኔታዎች

በልባቸው ከኃጢአት የነጹ፣ለበጎ ሥራ የነቁ፣ በሥራው ሁሉ የሚታመኑ፣ነገር የማይሠሩ፣፷ ዓመት የሞላቸው፣በአንድ ወንድ ጸንተው የኖሩ፣ በበጎ ምግባር ጸንተው ለመኖራቸው የተመሰከረላቸው ፣ ልጆቻቸውን በሥርዓት ያሳደጉ፣እንግዳ የሚቀበሉ፣ የቅዱሳንን እግር የሚያጥቡ ፣በደዌ በችግር ለተጨነቁት የሚራሩ ፣ በበጎ ሥራ ሁሉ ጸንተው የኖሩ ሴቶች ዲያቆናዊትነት ይሾማሉ ።(ፍትሐ ነገሥት ፯ ክፍል ፩ ድስቅ ፲፯ ፲፩፣ ፩.ጢሞቴዎስ ፭ ፣ ፱—፲ ።)



### ክፍል ፪

### ሥርዓተ ሢመተ ዲያቆናውያት

ዲያቆናውያት በአንብሮተ እድ አይሾሙም የሚሾሙት በቃል ብቻ ነው ፤
ማስረጃ «ወኢይግሥሥዎን ዘእንበለ በአንብሮተ እድ ባሕቲቱ» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፩ ድስቅ ፲፯ ። )

### ክፍል ፫

### የዲያቆናውያት ሥራ

ሀ. ዲያቆናውያት የሚሾሙት ከኤጲስ ቆጶሱ ወደ ሴቶች ለመላክ ፣ የሚጠመቁትን ሴቶች ከአንገት በታች ቅብዐ ቅዱስ እንዲቀቡ ፣ በጠቅላላው በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሴቶች ሊፈጽሙት የሚገባውን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲፈጽሙ ነው ፤(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፯ ክፍል ፩ ድስቅ ፲፯ ረስጣ ፶፱ ። )

ለ. ዲያቆናውያት ሴቶች አይባርኩም ዲያቆናውያት ሴቶች ዲያቆናትና ቀሳውስት የሚሠሩትን የክ

www.ethiopianorthodox.org

ሀነት ሥራ አይሠሩም ። ዲያቆናውያት ፤ ሴቶች የሚገቡበትን በር ብቻ ይጠብቃሉ ። «ይዕቀባ አንቀጸ ባሕቲቶ» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፰ ክፍል ፫ ረሰጣ ፶፬ ።)

ሐ. ዲያቆናዊት በሕዝቡ ዘንድ ክብር አላት «ወት ኩን ዲያቆናዊት ክብርተ በኀቤክሙ»

መ. ዲያቆናዊት እንደ ዲያቆናት «ተንሥኡ ጸልዩ» እያለች ጸሎት አታዝዝም ዲያቆን ሳያዛትም ምንም ነገር አትሠራም ፤ (ፍትሐ ነገሥት አን ቀጽ ፰ ክፍል ፫ በጻስ ፯ ።)

ሠ. ስለማናቸውም ጉዳይ ለመጠየቅ አንዲት ሴት ዲያቆናዊትን ሳትይዝ ብቻዋን ወደ ዲያቆን ወይም ወደ ኤጲስ ቆጶስ መሔድ አይገባትም ። ክልክል ነው ፤(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፰ ክፍል ፫ በጻስ ፯ ። )

ረ. ዲያቆናዊት ሴቶችን ልትገሥጽ ፥ልትመክር፥ ልታስተምር፥ ልትረዳቸው ይገባል ።(ፍትሐ ነገ ሥት አንቀጽ ፰ በጻስ ፵፬ ።)

ሰ. ዲያቆናውያት ቅስና አይሾሙም ቄስ፥አይባሉም፥ በቤተ ክርስቲያንም የማኅበር ጸሎት ጀማሪ ፈጻሚ አይሆኑም ።

ቀ. ዲያቆናውያት ቃላቸውን ከፍ አድርገው ጮኸው አይጸልዩም «ወኢይጸልያ በልዑል ቃል»(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፰ ክፍል ፫ ዶቅ ፲፩ ። )



## ተክሊል

ተክሊል ማለት ከለለ አከበረ ካለው ግሥ የወጣ ቃል ነው ። ይኸውም ክብር ማለት ነው ። ጸሎተ ተክሊል ወንድና ሴት ተስማምተው በሚያደርጉት ጋብቻ ላይ ካህኑ የሚሠራው መርዓዊና መርዓት ሁለቱ አንድ የሚሆኑበት መንፈሳዊ አገልግሎት ነው ። የጸሎተ ተክሊልፍጻሜ ጸሎተ ቅዳሴ ነው ። ከጸሎተ ተክሊሉ እያይዞ ጸሎተ ቅዳሴ ደርሶላቸው ሙሽሮች ሥጋውን ደሙን ይቀበላሉ ። ጸሎተ ተክሊል ተደርሶ ቊርባን ከቀረ ግን ተክሊሉ ፍጹም አይደለምና ጋብቻው አይጸናም «ወማዕሠረ ተዋስቦሰ ኢይከውን ወኢይትፌጸም ዘእንበለ በሀልዎተ ካህናት ወጸሎት ዘላዕሌሆሙ ወይመጥውዎሙ ቊርባነ ቅዱሰ በጊዜ ተክሊል ዘቦቱ ይትወሐዱ ክልኤሆሙ ወይከውኑ አሐደ ሥጋ በከመ ነገረ እግዚእነ ሎቱ ስብሐት ወዘ እንበለ ዝንቱ ኢይትኄለቁ ሎሙ አውስቦ» እንዲል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፬ መጅ ፩)

የጋብቻ ሥርዓት የሚፈጸምበት፥ካህናት ሙሽ ራውንና ሙሽራዪቱን አንድ የሚያደርጉበት ትእ ዛዝ እግዚአብሔርን የሚያጸኑበት ሥርዓት፥ ተክሊል ይባላል ።

ስለዚህ «ወንድ አባቱንና እናቱን ይተዋል ሚስቱንም ይከተላል ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ እንግዲህስ አንድ አካል ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም እግዚአ ብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለየው አይችልም»

www.ethiopianorthodox.org

ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሮአል ማቴዎስ ፲፱ ፡ ፫-፮ ፡ ዘፍጥረት ፪ ፡ ፳፬ ።

በቤተ ክርስቲያን በተክሊል ለሚደረገው ጋብቻ የሚጸለየው ጸሎት ይህን ትምህርት የተከተለ ነው

## የጋብቻ ተፈላጊነት

እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ በጋብቻ ሕግ እንዲኖሩ ሲያደርግ ስለ ፫ ነገር ነው ይኸውም

፩ኛ. ለመረዳዳት ነው

ማስረጃ «ሰውብቻውን ሊኖር አይገባውምና የምትረዳውን እንፍጠርለት» እንዲል(ዘፍ ፪ ፡ ፲፰።)

፪ኛ. ለመባዛትና ልጆችን ለማስገኘት ነው ።

ማስረጃ«ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልዕዋ ለምድር» እንዲል (ዘፍጥረት ፩.፳፰/፱ ፡ ፩ ።)

፫ኛ. ከዝሙት ግብር ለመጠበቅ ነው ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ «ወከመሰ ኢትዘምዉ ኵሉብእሲ ይንበር በብእሲቱ ወኵላ ብእሲት ትንበር በምታ» ብሎ አዝዞአል (፩ ፡ ቆሮንቶስ ፯ ፡ ፪ ።

## ክፍል ፪

## ማጨት

ሀ. ያመኑ ሰዎች ያላመኑትን አያገቡም ፤ ምእመናን ከምእመናን ይጋባሉእንጂበሃይማኖትከተለዩና ከአረማውያን መጋባት ክልክል ነው(ዘኒቅያ ፳፪)



ለ. ከ፲፭ ዓመት በላይ ዕድሜ ያላት ድንግል ከ፳ ዓመት በላይ ዕድሜ ያለው ድንግል ተጫጭተው ጋብቻቸውን መፈጸም ይችላሉ፣ በውዴታ የሰጡት ቃላቸውም ይጸናል ፤ ከዚህ ዕድሜ በታች ከሆኑ ግን አይጸናም ፤(ፍትሐ ነገ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፬ ምዕራፍ ፫) ክፍል ዳግም ጠስ ፳ እንዲህ ይላል «ወፍጻሜ መጠነ አካል ዘዕደው እሥራ ዓመት ወእመአኮ እሥራ ወሐምስቱ ዓመት ወለአንስትኒ አሠርቱ ወክልኤቱ ዓመት ወእመ አኮ አሠርቱ ወሐምስቱ ዓመት»

ሐ. ሁለቱ ዕጮኞች በወላጆቻቸውና በመምህረ ንስሓቸው የውዴታ ቃላቸውን ከገለጡ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሔዳሉ ከዚያም የጋብቻ ደንብ የሚያዘውን ይፈጽማሉ ።

መ. ሁለቱ ዕጮኞች ከመጋባታቸው አስቀድሞ በሚተጫጩበት ጊዜ ከሁሉ አስቀድሞ ሊጋቡ መፈቃቀዳቸውን ለኤጲስ ቆጶሱ ወይም ለቄሱ ይነግራሉ ።

ሠ. ኤጲስ ቆጶሱ ወይም ቄሱ መርምሮ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ደንብ ለጋብቻ የሚበቁ መሆናቸውን ከተረዳ በኋላ ይፈቅድላቸዋል

## ክፍል ፫

## ቃል ኪዳን (ቀለበት ማሠር)

ሀ. ለጋብቻ የተጫጩት ከጋብቻው ቀን አስቀድሞ ከቤተ ክህነት የተሰጣቸውን ማስረጃ በአቅራቢያቸው ላለው የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ አቅ

www.ethiopianorthodox.org

ርበው ቃል ኪዳናቸውን በቤተ ክርስቲያን ይፈጽ ማሉ ።

ለ. ሙሽራውና ሙሽራዪቱ ከዘመዶቻቸው ጋር በቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ለቃል ኪዳን በተ ሰጠው ሕግ መሠረት የቀለበቱን ሥነ ሥርዓት ያደ ርጋሉ በመተጫጨት የሰጡትንም የፈቃድ ቃል በመሐላ ያጸናሉ ።

## ክፍል ፬

## ሥርዓተ ተክሊል

ሀ. ጋብቻ ያለ ሥርዓተ ተክሊል ሊፈጸም አልተፈቀደም (ፍትሐ ፡ ነገ ፡ አንቀጽ ፴፬ ም ፡ ሐምስ ክፍል ዳግም መጅ ፩ ።)

ለ. ሥርዓተ ተክሊል ድሃና ባለጸጋ ጌታና ሎሌ እመቤትና ገረድ ካህንና ምእመን የማይለዩበት በድንግልና ለኖረ ሁሉ የሚፈጸም ሥርዓት ነው ።

ሐ. ተክሊሉ በሚደርስበት ቀን ሙሽራው ከዘመዶቹ ጋር ሙሽራዪቱም ከዘመዶቿ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔደው ሙሽራውና ዘመዶቹ በሰ ሜናዊ ማዕዘን ሙሽራዪቱና ዘመዶቹዋ በደቡባዊ ማዕ ዝን ሥፍራ ሥፍራቸውን ይዘው ይቆማሉ ።

መ. ከዚህ በኋላ በምዕራብ በኩል በመካከ ለኛው ክፍል ማለት በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት ባለው ዐውደ ምሕረት (ቅድስት) ላይ ሊቀ ዲያቆ ናቱ ሙሽራውና ሙሽራዪቱ ሥርዓተ ተክሊል የሚ



ፈጽሙበትን ምንጣፍ አንጥፎ ለሁለቱ የሚሆን መቀመጫ እንዲሁም አንድ ጠረጴዛና ሙሽሮቹ አንድ ሆነው የሚለብሱትን ነጭ መጐናጸፊያ የሚቀ ቡትን ዘይት የሚያቀዳጁዋቸውን አክሊላት ያዘጋጃል።

ሠ. ቀጥሎ ካህናቱ ሥርዓተ ተክሊሉን ማድ ረስ ይጀምራሉ ።

ረ. ከዚያም ካህናቱ ሥርዓተ ተክሊሉን አድ ርሰው ሲፈጽሙ ሙሽሮቹ አስቀድሰው ሥጋውን ደሙን ይቀበላሉ ጋብቻቸውን በሥጋው በደሙ ያጸናሉ ።

## ከጋብቻ በኋላ የባልና ሚስት አኑዋኑዋር

ሥርዓተ ተክሊል ከተነገረ ዘንድ ባልና ሚስት በኑሮዋቸው በመግባባት አንዱ የአንዱን ፈቃድ በመ ፈጸም እንዲኖሩ መጽሐፍ የሚሰጠውን ምክር ከዚህ ቀጥዬ አቀርባለሁ ።

ሀ. ባል ለሚስቱ የሚገባትን ሁሉ መጠበቅ ማድ ረግ ይገባዋል ፤ ሚስት ለባልዋ የሚገባውን መጠበቅ ማድረግ ይገባታል ። (፩ኛ ቆሮንቶስ ፯ ፡ ፫ ።)

ለ. ሚስት በኑሮ ሥርዓት ባልዋ ያዝባታል እንጂ በራስዋ አታዝም ባልም ሚስቱ ታዝበታለች እንጂ በራሱ አያዝም (፩ኛ ቆሮንቶስ ፯፡ ፬ ።)

ሐ. ለጾምና ለጸሎት ከተወሰነ ጊዜ በስተቀር ባልና ሚስት መለያየት የለባቸውም ሰይጣን ድል

www.ethiopianorthodox.org

እንዳይነሣቸው ተጠባብቀው መኖር ይገባቸዋል (፩ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፯ ፡ ፭ ።)

መ. ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትታዘዝ ሚስትም ለባሉዋ መታዘዝ ይገባታል ፤እንዲሁም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንንን እንደ ወደዳት ራሱንም ለሞት አሳልፎ እንደ ሰጠላት እንደዚሁም ወንድ አካሉ ናትና ሚስቱን መውደድ መርዳት ይገባዋል፤ (ኤፌሶን ፭ ፳፪—፴፫ ። ፩ኛ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፩-፯ ።

ሠ. ባልና ሚስት አንድ ልብ አንድ አፍ ሆነው በመተማመን መኖር ይገባቸዋል እንጂ በአሳብ መለያየት መተማማት የለባቸውም (፩.ጴጥ ፫፡፰።)

ረ. ባልና ሚስት በፅንስ ፡ በሕርስ ፡ በትክትጊዜ፡ በሰንበት ፡ በበዓላት ፡ በአጽዋማት ወራት መጠበቅ ይገባቸዋል ።

«ወለእመ ኮነ ብእሲ ዘይዴመር ምስለ ብእሲቱ እምድኅረ ተከሥተ ፅንሳ ወዝንቱ ኢርቱዕ ወኢብውሀ ሊቀ ለዝንቱስ ኢይትፈቀድ ነገር በአንቲአሁ» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፬ በስ ፲፩) ።

## ፍቺ እንዳልተፈቀደ

ሀ. ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ መፋታት በልዩ ልዩ ምክንያት ቃል ኪዳናቸውን ማፍረስ አይገባቸውም ።

«የሕፃንነት ሚስትህን አትፍታ» ሲል ሚልክያስ የተባለው ነቢይ ተናግሮታል ። (ሚልክያስ)



፪,፲፬—፲፯ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለየው አይችልም» ብሎአል (ማርቆስ ፲ ፡ ፪-፱) ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም«ሴት ከባልዋ አትለይ ወንድም ከሚስቱ አይለይ ሁላችሁም በጌታችን ትእዛዝ አንድ ሁናችሁ ኑሩ»ሲል አስተምሮዋል ፩ኛ. ቆሮንቶስ ፲፩.፲፩ እንዲሁም « በሚስት ታሥረህ እንደሆንህ መፋታትን አትሻ» ብሏል ፩ኛ. ቆሮንቶስ ፯ ፡ ፳፯ ።

ለ. ባልና ሚስት በድንገተኛ ግጭት በዕለት ቁጣ ቢለያዩ መታረቅ አለባቸው አንታረቅም ካሉ ግን በእየራሳቸው ንጽሕናቸውን ጠብቀው መኖር አለባቸው እንጂ ሌላ ማግባት የለም ። «ሴት ከባልዋ አትፋታ ብትፋታም ንጽሕናዋን ጠብቃ ትኑር አለዚያ ግን ከባልዋ ጋር ትታረቅ ወንድም ሚስቱን አይፍታ» እንዳለ (፩ኛ ቆሮንቶስ ፯ ፡ ፲—፲፩ ።

ሐ. ማንኛውም ሰው ሚስቱን ሊፈታ ቢወድ ከካህናት አንዱ ነውሩዋን የሚናገር ደብዳቤ መጻፍ የለበትም ከጻፈ ግን መልሶ እስከሚያስታርቀው ድረስ ከምእመናን ይለያል ።

«ወለእመ ፈቀደ አሐዱሂ ከመ ይድኃር ብእሴቶ ወጸሐፈ አሐዱ እምካህናት መጽሐፈ ኅዳጋቲሃ ይሰደድ እስከ ይመይጣ ለተዋስቦ ወያስተሳልሞ» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፱ ረስጠጅ ፳፩)

www.ethiopianorthodox.org

## ፍችና ሁለተኛ ጋብቻ

ሀ. ሁለተኛ ጋብቻ የሚፈቀደው ሚስት ወይም ባል በሞት ሲለዩ ብቻ ነው ከዚህ በስተቀር ሁለተኛ ጋብቻ አይፈቀድም ባልና ሚስት በሞት መለያየት ከደረሰባቸው ግን ወደ ኋላ የቀረው ንጽሕናውን ጠብቆ መኖር የማይቻለው ከሆነ ሁለተኛ ማግባት ይችላል ሁለተኛዋም ከሞተች እስከ ፫ ጊዜ ድረስ ማግባት ይችላል ፤

ሴት ባልዋ በሕይወት ሳለ በሕግ የጸናች ናት፤ ባልዋ የሞተ እንደሆነ ግን ለባሉዋ ከገባች ለት ቃል ኪዳን ነፃ ናት ። ባሉዋ በሕይወት ሳለ ከሌላ ወንድ ብትደርስ ዝሙት ይሆንባታል ። ባሉዋ የሞተ እንደሆነ ግን ሌላ ብታገባ ዝሙት አይሆንባትም ሰሰነች አትባልም (፩ ቆሮ ፯ ፡ ፴፱ ፡ )።

ወንድ ሚስት የሚያገባው የሚስቱ ሙት ዓመት ከአለፈ በኋላ ነው ሴት ባልዋ ከሞተ ከ፲ ወር በኋላ ታገባለች ።

«ወኢያውስብ ዘእንበለ ይኅልፍ አሐዱ ዓመት እምቅድመ ፲ቱ አውራኅ እምከመ ሞተ ምታ ኢትረስ ንዋየ ምታ» (ፍት ነገ አንቀጽ ፳፬ ።) «ወእመሰ ያፈ መንጢጥ ዘኢነባቢ ይትገሐሥ እምአውስቦ ዳግማዊ እፎ እንከ ፈድፋደ ይደሉ ለእንስሳ ነባቢ» ።



ፍሬ ነገር የማይናገር ያፈ መንጢጥ (ርግብ) ከ ሁለተኛ ጋብቻ የሚከለከል ከሆነ ፍሬ ነገር የሚናገር ሰውማ ከሁለተኛው ግቢ መከልከል እንደምን አይገባውም?» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፬ በስ ፺፫) ።

«ወበእንተ ዝንቱ ፍና ይደሉ ዐቂበ ዛቲ ሕግ እስመ ይእቲ ታወርዶሙ ለክቡራን እምክብሮሙ ዘውእቶሙ ካህናት ወይእቲ ሎሙ ትከውን ምንንተ» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፬ ።)

ለ. ከላይ ከተጠቀሰው በሞት ምክንያት ከሚደረገው መለያየት ሌላ ወንድ ሚስቱን መፍታት የሚገባው ስታመነዝርበት ብቻ ነው ወይንም ሴት ባሉዋን መፍታት የሚገባት ሲያመነዝር ባት ብቻ ነው ማንኛውም ወገን ማለት ወንድም ሆነ ሴት በዝሙት ምክንያት ከፈታ በኋላ በዝሙት ምክንያት የተፈታችውን ወገን ማግባት አልተፈቀደለትም ማግባት የሚቻለው ንጽሕናውን ጠብቆ በቊርባን ተወስኖ የኖረውን ወገን ብቻ ነው (ማቴዎስ ፭ ፡ ፴፩-፴፪ ። ፲፱ ፡ ፯-፱) ።

ሐ. ለሁለተኛ ጋብቻ መጽሐፈ ተክሊል አይጸለይም ሥርዓተ ተክሊል አይደረግም የሚጸለየው ፍትሐት ዘወልድና ጸሎተ ንስሓ ብቻ ነው ። «ወኢይጸልዩ ላዕለ አውስቦ ዳግማዊ ዘውእቱ ጸሎተ ተክሊል ወአኮ ጸሎተ ፍትሐት» እንዲል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፱ ክፍል ፬ ሥርዋጽ ፳ በስ ፸፪ ።)

www.ethiopianorthodox.org

«ወአውስቦሰ ዳግሚት ካልዕት ተሐጽጽ እምቀዳሚ ወለዛቲሰ ተሠርዐ በቀኖናት ከመ ኢትኩን ላቲ በረከተ ተክሊል አላ ይግበሩ ጸሎተ አስተስርዮ»(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፬ ዕንቈራ ፲፰)።
« ወተጋብኦሰ ማእከለ አውስቦ ዳግማዊ እው ዘይበዝኅ ኢይደሉ እስመ ውእቱ ዝሙት ክሡት - - -» (እንዲል ፍትሐ ነገሥት አን ፳፬) ።

## ሦስተኛ ጋብቻ

ሀ. ሦስተኛ ጋብቻ ፈጽሞ የተናቀ ነው ነገር ግን ከላይ እንደተገለጠው ሚስቱ ከሞተችበት አንድ ሰው ለ፫ኛ ጊዜ በሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት የንስሓ ጸሎት ተደርሶለት በቤተ ክርስቲያን ያገባል ከ፫ ጊዜ በላይ ማግባት ግን ለክርስቲያን አልተፈቀደም ።

« ወአውስቦሰ ሣልስ ምኑን ውእቱ ወአልቦ በኀቤነ እምድኅረዝ አውስቦ ሕጋዊ » እንዲል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፬) ።

«ወለእመቦ ዘአውሰበ ዘኢኮነ እምሕግነ ይትከላዕ ዓመተ ወዘአውሰበ ራብዐ ኢይቅረብ» (ፍትሐ ነገሥት ፳፬ ።)

ለ. መአስባን ማለት አግብተው የፈቱና በንስሓ የተመለሱ ምእመናን ጋብቻቸውን በሥርዓተ ጸሎትና በቅዱስ ቍርባን ለመፈጸም ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚመጡበት ጊዜ ቄሱ ከሁሉ አስቀድሞ ለመጋባት የተፈቃቀዱበትን የሁ



ለቱን ሰዎች ጋብቻ የሚከለክል ምክንያት አለመኖሩንና በእነርሱም በኩል እስከ መጨረሻው መለያየትን የሚያስከትል ስምምነት በመካከላቸው መኖሩን ይመረምራል ከመጋባት የሚከለክላቸው ምክንያት አለመኖሩንና ስምምነታቸው ፍጹም መሆኑን በሚገባ ከተረዳ ጸሎት ያደርስላቸዋል ከጸሎቱም በኋላ የክርቶስን ሥጋውን ደሙን ያቀብላቸዋል ።

ሐ. በሚስት ላይ ሚስት ማስቀመጥ ክልክል ነው።
« ወኢያንብር ብእሲ ክልኤተ አንስተ በምክንያተ ተድላ» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፬)

መ. ካህን ሁለተኛ ቢያገባ ክህነቱ ይሻራል ሦስተኛ ቢያገባ ግን አልተፈቀደለትም ርኩስ ነው ።
«ወለእመ ኮኑ ዕደው ካህናት ይደቁ እማዕርጊሆሙ ወእምድኅሬሁሰ ለእመ ደገሙ ይከውኑ ርኩሳነ» ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፬ ም.፩ ፤ ክፍል ፫ ቍጥር ፩—፮ ኒቅያ ፲፱ ።

ሠ. ከወንድ ዝሙት ቅጣት ይልቅ የሴት ዝሙት ቅጣት ይበልጣል ።

«ወይደሉ ከመ ይጽናዕ ኵነኔ ዝሙታ ለብእሲት ፈድፋደ እምብእሲሃ» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፬ ሥርዋፅ ፳፬ ቍ ፴፩ ።)

## የሥርዓተ ተክሊል አፈጻጸም

የሥርዓተ ተክሊል አፈጻጸም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ ተሻሽሎና ተስተካክሎ ሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ/ም በታተመው መጽሐፈ «ተክሊል

www.ethiopianorthodox.org

የተገለጸ ስለሆነ አንባቢ ይህንኑ መጽሐፍ በመመልከት በቀላሉ ሊረዳው ስለሚችል ከዚህ ላይ በድጋሚ ማተት አላስፈለገም ።

## የሥርዓተ ተክሊል ትርጉም

ሀ. የሙሽራውና የሙሽራዪቱ ተዋሕዶ የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ተዋሕዶ ምሳሌ ነው»ዐቢይ ውእቱ ዝ ነገር አንሰ እብሎ ላዕለ ክርስቶስ ወላዕለ ቤተ ክርስቲያን» ኤፌሶን ፭፡ ፴፪ ።

ለ. ሙሽሮች በቃል ኪዳናቸው ጊዜ ቀለበት የሚያደርጉት የቃል ኪዳንና የሃይማኖት ምልክት በመሆኑ ነው ።

ሐ. የአመኑ ሰዎች ያላመኑትን እንዳያገቡ የተደረገበት ምክንያት በሃይማኖት አንድ ስለአልሆኑ ነው«ኢተሀብ ወለተከ ለአሕዛብ ወኢትንሣእ ወለቶሙ ለአሕዛብ» ተብሎአልና (ዘዳግም ፯፡ ፫-፯ )

መ. በሥርዓተ ተክሊል ላይ ሙሽሮች የሚለብሱት አንድ ልብስ አንድ አካል ለምታደርጋቸው ጸጋ መብቃታቸውን የሚያስረዳ ነው ።

## ቀንዲል

ቀንዲል ሕሙማን እየተቀቡ የሚፈወሱበት ቅብዕ ነው ፤ ቀንዲል ወይም ቅብዐ ጸሎት ከን



ዱሕ ወይራ ዘይት ይሠራል ይህ ቅብዕ በእግዚአብሔር ጸጋ በቄሱ ጸሎት የማዳን ኃይል ስላለው በቅዱስ ያዕቆብ መልእክት እንደ ተጻፈው ሕሙማን ይፈወሱበታል ።

ቀንዲል ሐዋርያት ይሠሩበት ነበር «በወጡም ጊዜ አስቀድመው ንስሓ አስተማሩ ንስሓ ይገቡ ዘንድ እጅግም ሰይጣናትን አስወጡ በዘይትም ብዙ ድውያንን ቀቡ አዳኑዋቸውም»ማርቆስ ፮ ፡ ፲፫ ። )

«ማንም ከእናንተ ቢታመም የቤተ ክርስቲያንን ቀሳውስት ይጥራ ይጸልዩለትም በዘይትም ይቅቡት በጌታ ስም የሃይማኖት ጸሎት ድውይን ትፈውሰዋለች ጌታም ያሥነሣዋል ኃጢአትም ሠርቶ እንደ ሆነ ትሰረይለታለች» (ያዕቆብ ፭ ፡ ፲፬-፲፮ ።)

በዚህ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ድውያንን ለመፈወስ ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እየጸለየች በዚህ ቅብዕ ሕሙማንን ትቀባለች ።

www.ethiopianorthodox.org

## ሥርዓተ ቀንዲል

ሀ. ቀንዲል ወይም ቅብዐ ድዉይ በቢልቃጥ ወይንም ቀርን ቅብዕ ሁኖ ከመንበር ይቀመጣል ።

ለ. ካህኑ መጽሐፈ ቀንዲል ደግሞ የበሽተኛውን አካል በመስቀል ምልክት ይቀባዋል ።

ሐ. የሚቀቡት የአካል ክፍሎች ግንባሩን ከ፪ ቦታ ፊቱን ከ፪ ቦታ ሽንንቡቱን (አገጩን) ቀኝና ግራ እጁን በውስጥም በወጭም ሁለት እግሩን ቢቻል ታላላቅ ሕዋሳቱን ሁሉ ያለዚያም ለጊዜው ከሚያመው አካሉ ላይ ይቀበዋል ተፈጸመ ። እንሣስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን ።



| ጥቅስ | ትርጕም |
|---|---|
| ማቴ | የማቴዎስ ወንጌል |
| ዮሐ | የዮሐንስ ወንጌል |
| ፩. ጴጥ | መጀመሪያው የጴጥሮስ መልእክት |
| ዘፀ | ኦሪት ዘፀዓት |
| ማር | የማርቆስ ወንጌል |
| ሉቃ | የሉቃስ ወንጌል |
| ፍት ነገ | ፍትሐ ነገሥት |
| ዕብራ | የዕብራውያን መልእክት |
| ዘዳ | ኦሪት ዘዳግም |
| በደስ | አቡሊዲስ |
| ዶቅ | የሎዶቅያ ሲኖዶስ |
| ረስጣ | ቀሌምንጦስ አንደኛ |
| ድስቅ | ዲዲስቅልያ |
| ፩ ቆሮ | መጀመሪያው የቆሮንቶስ መልእክት |
| ዘሌዋ | ኦሪት ዘሌዋውያን |
| ዘኒቅያ | የኒቅያ ሲኖዶስ |
| መዝ | መዝሙረ ዳዊት |
| ዮሐ አፈ | ዮሐንስ አፈወርቅ |
| በስ | ባስልዮስ |
| ዘፍ | ኦሪት ዘፍጥረት |
| ኤፌ | የኤፌሶን መልእክት |
| ረስጠብ | ሁለተኛ ቀሌምንጦስ |
| ጴጥ | ጴጥሮስ |

www.ethiopianorthodox.org